# ምዕራፍ 5

## ጳውሎስ ስለ መሪነት የሰጠው ትምህርት

«ማንም ኤጲስ ቆጶስነትን ቢፈልግ መልካምን ሥራ ይመኛል» የሚለው ቃል የታመነ ነው። እንግዲህ ኤጲስ ቆጶስ እንዲህ ሊሆን ይገባዋል:- «የማይነቀፍ፥ የአንዲት ሚስት ባል፥ ልከኛ፥ ራሱን የሚገዛ፥ እንደሚገባው የሚሠራ፥ እንግዳ ተቀባይ፥ ለማስተማር የሚበቃ፥ የማይሰክር፥ የማይጨቃጨቅ ነገር ግን ገር የሆነ የማይከራከር፥ ገንዘብን የማይወድ፥ ልጆቹን በጭምትነት ሁሉ እየገዛ የራሱን ቤት በመልካም የሚያስተዳድር። ሰው ግን የራሱን ቤት እንዲያስተዳድር ባያውቅ የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን እንዴት ይጠብቃታል? በትዕቢት ተነፍቶ በዲያብሎስ ፍርድ እንዳይወድቅ አዲስ ክርስቲያን አይሁን። በዲያብሎስ ነቀፋና ወጥመድም እንዳይወድቅ በውጭ ካሉት ሰዎች ደግሞ መልካም ምስክር ሊኖረው ይገባዋል፥» 1ጢሞ.3፡27።

እንደ ጳውሎስ የታማኝ አገልጋይነትን መመዘኛዎች ለመዘርዘር የሚችል ማን ነው? ጳውሎስ ከራሱ መንፈሳዊ ልምምድና በውስጡ ባደረው መንፈስ ቅዱስ አማካይነት መልዕክት ያስተላልፍ ነበር። በአንድ ትውልድ ሲሠራባቸው የነበሩ መንፈሳዊ መለኪያዎች ከሌላም ትውልድ ጠቃሚ ሊሆኑ ይችላሉ። በሠለጠነው ባሁኑ ዘመንም ቤተ ክርስቲያን በተመሠረተችበት ወቅት በተሰጡት መንፈሳዊ መለኪያዎች እንጠቀምባቸዋለን። ጳውሎስ የሰጣቸው የታማኝ አገልጋይ መመዘኛዎች በሙሉ የግድ መሟላት ያለባቸው ነጥቦች እንጂ እንደ ሰው ፈቃድ ተደርገው በአማራጭነት የተሰጡ አይደሉም።

ኤጲስ ቆጶስና ሽማግሌ የሚሉት ሁለት ቃላት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ አንድ ዓይነት ሥራ ለሚሠሩ ሰዎች የተሰጡ መጠሪያ ስሞች ናቸው። ሽማግሌ የሚለው ቃል የሚያመለክተው ክብሩንና ሥልጣኑን ነው፤ ኤጲስ ቆጶስ የሚለው ደግሞ የሚያመለክተው ተግባሩንና አገልግሎቱን ነው። በሌላ አነጋገር አንዱ ስም ክብሩንና ሥልጣኑን ሲያመለክት ሌላው ደግሞ ግብሩን ያመለክታል ማለት ነው። ይህ ገለጻ የተመሠረተው ጳውሎስ ተመሳሳይ ሥራ የሚሠሩትን አንድ ዓይነት ሰዎች አንዴ ሽማግሌዎች ሌላ ጊዜ ደግሞ ኤጲስ ቆጶሳት ብሎ በጠራባቸው በሐዋ.20፡17 እና 28 ላይ ነው። ኤጲስ ቆጶስ የሚለው መጠሪያ በሐዋ.20፡1718 ውስጥ ከሚገኘው ትርጉሙ በላይ ተጋንኖ የተሠራበት ከጳውሎስ ዘመን በኋላ ነው።

በዚህ ምዕራፍ መጀመሪያ ላይ የተጠቀሰው 1ጢሞ.3፡27 የመንፈሳዊ መሪነት ችሎታዎችን በዝርዝር ገልጿቸዋል።

# ታማኝ አገልጋይ ከኅብረተሰብ ጋር ያለውን

# ግንኙነት የሚመለከቱ መመዘኛዎች

አገልጋይ በቤተ ክርስቲያን በሚገኙ ምዕመናን ዘንድ የማይነቀፍ ሆኖ መገኘት አለበት። ጸባዩ ከሌላው ጋር በአደባባይ የሚያጋጨው ወይም የሚያስነቅፈው መሆን የለበትም፤ የሚያጉረመርሙና የሚያሾከሹኩ ሰዎች ቦታ አያገኙም። ክስ ቢቀርብበትም እንኳ በሕይወቱ ነቀፋ ስለሌለ ክሱ ተቀባይነት ሊያገኝ አይችልም። ተቃዋሚዎቹ ሌሎችን በማሳደም ክፉ ነገር ሊያስወሩበት የሚያስችላቸው ምንም ዓይነት የተቃውሞ በር ሊከፍትላቸው አይገባም።

በውጭ ባሉት ሰዎች ዘንድም ጥሩ ምስክርነት ሊኖረው ይገባል። ከክርስቲያን ጋር በዕለታዊ ኑሮው አብሮ የሚኖርና የሚሠራ ሰው፥ ወይም ከቤተ ክርስቲያን ውጪ ከክርስቲያን ጋር የሚሠማራ ሰው የክርስቲያኑን ጸባይ እውነተኛነት ጥርት አድርጎ ይመለከታል። ታማኝ አገልጋይ ጥሩ ምስክርነት እንዲኖረው የሚያስፈልግበት ምክንያት ግልጽ ነው። የዚህ መጽሐፍ ጸሐፊ የሚያውቀው ከቤተ ክርስቲያን ውጪ የሚሠራ አንድ የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌ ነበር፤ ይህ ሰው አንዳንድ ጊዜ እሑድ እሑድ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንዲሰብክ ይጋበዝ ነበር። እሑድ ዕለት ሰብኮ እንደሆነ ሰኞ ሥራው ሲገባ የሚያሳየው በጣም መጥፎ ሁኔታ ነበር። ስለዚህ በእርሱ ድርጅት ውስጥ ተቀጥረው የሚሠሩ ሠራተኞች ሰኞ ዕለት መጥፎ ሁኔታ ካሳያቸው «ትናንት ስብከት ሰብኳል፤ እርሱ ብሎ ሰባኪ!» ብለው ይተቹበት ነበር። ከዚህም ሁኔታ የተነሣ የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች ሠራተኞቹን ወደ ክርስቶስ ሊያመጣቸው አልቻለም።

አማኝ ያልሆኑ ሰዎች ከክርስቲያኖች ልዩ ሥነ ምግባራዊ ኑሮ ስለሚጠብቁ ክርስቲያን የሆነ ሰው በፊታቸው ቅድስና በተሞላው አኗኗር ሲራመድ ከተመለከቱ፤ ትችት መተቸታቸውን ትተው በተመሳሳይ ሕይወት የመኖር ምኞት ያድርባቸዋል፤ እርሱንም ለመምሰል ምኞት ይኖራቸዋል። ስለዚህ የአንድ ሽማግሌ ጸባይ በውጭ ባሉት ዘንድ እንኳ መታፈርና መከበር የሚያተርፍ መሆን አለበት። ይህ በሚሆንበት ጊዜ መንፈሱ ይበልጥ ስለሚነቃቃ የበለጠ መልካም አርአያ በመሆን የመልካም ተግባር ምሳሌ ለመሆን ይደፋፈራል። ስለዚህ ከሕግ አጥባቂና ከትዕዛዝ ደርዳሪ ሆኖ ከመገኘት ይልቅ አርአያ ሆኖ መገኘት ይበልጥ ኃይል አለው።

# የታማኝ አገልጋይ ሥነ ምግባር መመዘኛዎች

መንፈሳዊ መመሪያዎችና የሥነ ምግባር ሥርዓቶች ርካሽና የማይረቡ ተደርገው በሚቆጠሩበት ዓለም ውስጥ መንፈሳዊ አገልጋይ የሆነ ሰው ጠባዩን አሳምሮ የማይነቀፍ ሆኖ መገኘት አለበት። በአንዲት ሚስት ብቻ ተወስኖ መኖር አጥጋቢ እንዳልሆነ ተደርጎ በሚገመትበት ኅብረተሰብ ውስጥ ቢሆንም «የአንዲት ሚስት ባል» ሆኖ መኖር አለበት። ይህ አባባል በሰዎች ዘንድ የተለያየ ትርጉም ቢሰጠውም መንፈሳዊ አገልጋይ ከሥነ ምግባር ጸባዩ አንፃር ነቀፋ የማይገኝበት ሊሆን እንደሚገባ እንገነዘባለን። ሰው በጋብቻው በሁሉ አንዲትና ብቸኛ ለሆነችው የትዳር ጓደኛው ታማኝ መሆን አለበት። ይህ ቀረህ በማይባል የተሟላ ሥነ ምግባር የታነፀ ጸባይ ሊኖረው ይገባል።

ራሱን የሚገዛ ሰው «ለብዙ ወይን ጠጅ የማይገዛ» ወይም ይህን በመሳሰሉት ሱሶች ያልተጠመደ መሆን አለበት። የመጠጥ ሱስ ቀስ በቀስ ሥር ሊሰድበት አይገባም። ምክንያቱም

የመጠጥ ሱስ ቀስ በቀስ ሥር ከሰደደበት ሰካራም ሆኖ ነገርን ሁሉ ሊያበላሽና ሊያዛባ ስለሚችል ነው። ጠጭና ሰካራም ሰው በኅብረተሰቡ ዘንድ ክብሩን ያጣና ወራዳ ነው። ታዲያ የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌ በማያምኑ ሰዎች ዘንድ ይህን ያህል ከቀለለ በክርስቲያኖች ዘንድ ምን ያህል የበለጠ የተናቀ ይሆን? መንፈሳዊ አገልጋይ ምስክርነቱን የሚያበላሹትንና መንፈሳዊ አቋሙን የሚያናጉትን ነገሮች በድብቅ ከመፈጸም መጠበቅ ይኖርበታል።

## የአገልጋይን አስተሳሰብ የሚመለከቱ መመዘኛዎች

መንፈሳዊ አገልጋይ ጥንቁቅና አስተዋይ የሆነ አዕምሮ ያለው መሆን አለበት። ይህም ሲባል ለውየው ራሱን የሚገዛና የሚያደርገውን ነገር በማስተዋልና ቅን በሆነ አስተያየት የሚፈጽም ጨዋ ሰው መሆን አለበት ማለት ነው። አንድ መንፈሳዊ ሰው ስለዚህ ነገር ሲናገሩ «ጥንቃቄ የአዕምሮ መቆጣጠቂያና የምኞት ልጓም ነው» ብለዋል። ግሪኮች ራስን የመግታት ችሎታ ታላቅ ጥቅም አለው ብለው ያምናሉ። በእነርሱ አስተሳሰብ ሰውን ከቁጥጥር ውጪ እንዳይሆን የሚያደርገውና እንዲሠለጥን ተደርጎ በቁጥጥር ሥር ያዋለው አዕምሮ ነው፤ በቁጥጥር ሥር የዋለና የሠለጠነ አዕምሮ ድንገተኛ ከሆኑ ስሜቶች የተነሣ ወደ መወላወል አይመጣም። ጥንቁቅ የሆነው ሰው አካሄድ የተስተካከለ ይሆናል። ለምሳሌ ያህል ድፍረት በጉብዝናና በፍርሃት መካከል ያለ ነገር ነው ይባላል። እንዲሁም ንጽሕና በቅድስናና በርኩሰት መካከል ነገር ነው ይባላል። ስለዚህ ይህንን የመሰለ አስፈላጊ የሆነ ችሎታ ያለው መሪ ሕሊናውንና የቀረውን የሕይወቱን ክፍል ሊቆጣጠርና ሊገታ የሚችል ሰው ነው።

በውጭ ሁናቴውም ማለት ባለባበሱ ዝርክርክ ያልሆነ፥ ቆፍጣናና ክቡር ሰው ሊሆን ይገባዋል። ግራኪ ሕይወት በአግባብ የሚያስብ አዕምሮ ውጤት ነው። ይህ ሕይወት የተስተካከለ እንደመሆኑ መጠን እግዚአብሔር የሚወደውን ትክክለኛነትንና ውበትን ያንጸባርቃል።

በአስተሳሰቡም ሆነ በመንፈሳዊ ሕይወቱ ለማስተማር የሚበቃ ሰው መሆን ይገባዋል። ይህም ችሎታን ብቻ የሚገልጽ ሳይሆን ምሳሌ ሆኖ ለማስተማር መዘጋጀትንም ያሳያል። በንግግሩም በኩል መንፈስ ቅዱስ ያስተማረውን ነገር ለሌሎቹ ለማካፈል መንፈሱ የሚገፋፋው ሰው መሆን ይገባዋል። ሌሎቹን ማስተማር ተግባሩ የሆነ ሰው ራሱ ደግሞ የእግዚአብሔርን ቃል የሚማር ተማሪ መሆን አለበት። የእግዚአብሔርን ቃል ለሌሎች በሚገባ ለማስተማር የማይችል ሰው ለሽምግልና የሚበቃ ሰው አይደለም። መንፈሳዊ አገልጋይ ከበታቹ ያሉትን ሰዎች በጥቂቱም ሆነ በብዙው የማስተማር ኃላፊነት አለበት። ለሌሎቹም የሚሰጠው መመሪያ ነቀፋ ከሌለበት ሕይወት የሚፈልቅ መሆን አለበት።

አንድ የእግዚአብሔር ሰው እንዲህ በማለት ተናገሩ፡- «በመካከላችን የሰውን ፍላጎትና ጥማት ተረድተው አስፈላጊውን መንፈሳዊ ምግብ የሚያቀርቡ አስተማሪዎች ምን ያህል ያስፈልጉን ይሆን? ሐኪም የበሽተኛውን ችግር አውቆ ትክክለኛውን መድኃኒት በመስጠት እንደሚረዳው ሁሉ መምህራንም የአማኞችን የልብ መሻት ተመልክተው በቃሉ ልባቸውን ለመጠገን የሚታገሉ መሆን ይገባቸዋል። በምእመናን ልብ አልፎ አልፎ ልክ እንደ ሥጋ ደዌ የሚያስጨንቃቸው ችግር ስለሚኖር ኢየሱስ ራሱ ይፈውሳቸዋል። ዶክተር ለእያንዳንዱ በሽተኛ ተመሳሳይ መድኃኒት እንደማይሰጥ ሁሉ ታማኝ አገልጋዮችም ለእያንዳንዱ ሁኔታ ተመሳሳይ ምክር ሊያቀርቡ አይችሉም። የእግዚአብሔርን ቃል በትጋት ማጥናትና ሕይወታችን በመንፈስ ቅዱስ የተዋበ እንዲሆን መጸለይ አለብን።»

ጆን ወስሊ የተባሉት የቤተ ክርስቲያን አገልጋይ ከፍ ብሎ በተጠቀሰው አኳኋን ያስተዳድሩ ነበር። ምንጊዜም የትምህርትን አስፈላጊነት አያንቋሽሹም ነበር። በአካባቢያቸው ይኖሩ የነበሩትን ሰዎች የማስተዋል ችሎታ እንዲሁም ሥነ ምግባራዊና መንፈሳዊ ሁኔታቸውን ማሳደግ የዘወትር ፍላጎታቸው ነበር። ስለዚህም በማንኛውም ቀላል በሆነ ጊዜያዊ ቀድላ አይደለሉም ነበር። የአዕምሯቸው ከፍተኛ አስተሳሰብና ችሎታም በጊዜያቸው ከነበሩ ምሁራን ሁሉ በላቀ ደረጃ ላይ አስቀምጧቸው ነበር። እርሳቸውም በጊዜው ከፍተኛ የሥነ ጽሑፍ ዕውቀት ነበራቸው። አንድ በጊዜው ዝነኛ የነበረ ሰባኪ የጆን ወስሊን አቋም ሲያወሳ «በሕይወቴ ዘመን በስብከት አቀነባበርና አቀለጣጠፍ እንዲሁም በአቀራረብ ስልትም ሆነ በቃላት አሰካክ እኚህን ሰው የሚወዳደራቸው በጭራሽ አላጋጠመኝም» በማለት ተናግሯል። ያም ሆነ ይህ እኚህ ሰው የወደዱት አንድ መጽሐፍ ብቻ ነው። በዚህ ሁሉ ግን ሁለንተናን ለእግዚአብሔር በመስጠት ረገድ ተወዳዳሪ የሌላቸው ምሳሌ በመሆን ሲታወሱ ይኖራሉ።

## የታማኝ አገልጋይን የግል አቋም የሚመለከቱ መመዘኛዎች

ክርስቲያኖችን የሚያገለግል ሰው ጸበኛ ያልሆነ፥ ጨዋና ራሱን የሚገዛ ሰው መሆን ይኖርበታል። ዘወትር የሚጨቃጨቅ ሳይሆን ተወዳጅ፥ ረጋ ያለ፥ ቁም ነገረኛ፥ ተግባቢና የሌሎችን ምክር የሚቀበል ሰው ሊሆን ይገባል። ይህ የራስን አቋም የመጠበቅ ችሎታ ተወዳዳሪ በሌለው አኳኋን የአገልጋዩን መልካም ጸባይ አጉልቶ ያሳየዋል። አንድ ሰው የራስን አቋም መቆጣጠር ስለተባለው ነገር ሲናገሩ «ሳያውቅ በተደጋጋሚ ስህተት በመሥራት የሚሳቀቁትን ሰዎች የሚያቃናቸውና የሚያስተካክላቸው ገርነት የተሞላበት መንፈስ ነው» ብለዋል። አርስቶትል በተባለው ፈላስፋ አስተሳሰብ ይህ ዓይነት ጸባይ ያለው ሰው ከክፉ ነገር ይልቅ መልካምን ያስታውሳል፤ ካደረገው መልካም ሥራ ይልቅ ያገኘውን ነገር ያስታውሳል። እንዲህ ዓይነቱ አገልጋይ ማንኛውም ችግር በሚፈጠርበት ጊዜ ነገሩን በቸልታ ከማሳለፍ ይልቅ በእርጋታ ተመልክቶ በሰላም እንዲረጋጋና በመልካም መንገድ እንዲስተካከል ያደርጋል።

ከዚህም በተጨማሪ እንግዳ ተቀባይና የባይተዋሮች ወዳጅ መሆን ይገባዋል። ይህንን አገልግሎት በመስጠቱና በዚህ መንገድ ጌታን የማገልገል ዕድል በማግኘቱ ደስ ሊሰኝ ይገባዋል እንጂ አገልግሎቱን እንደ ቀላል ነገር ቆጥሮ ችላ ሊል አይገባም። ከዚህ በፊት በተጻፈ በአንድ መጽሐፍ ውስጥ ታማኝ አገልጋይ እንግዳ ተቀባይና የእግዚአብሔር አገልጋዮችን ዘወትር በፍቅር ተቀብሎ የሚያስተናግድ መሆን እንዳለበት ተነግሯል።

ጳውሎስ እንግዳ ስለመቀበል በጻፈበት ዘመን ለእንግዶች መደረግ የነበረበት አቀባበል አሁን ካለንበት ዘመን ይልቅ እጅግ አስፈላጊ ነበረ። ሆኖም በዚያ ወቅት ይደረግ የነበረው አቀባበል አሁንም ከመንፈሳዊ አገልጋይ ይጠበቃል። ከዚህ አንጻር ይህ የማስተናገድ ኃላፊነት ከመንፈሳዊ አገልጋዩ ይልቅ በሚስቱ ላይ ያተኩራል። የጥንት ዘመን ሆቴሎች እጅግ በጣም ጥቂት ነበሩ፤ ለዚያውም ደግሞ እነዚሁ ጥቂቶቹ በርኩሰትና በፍትወት ተበክለው ነበር። አረማውያን ክርስቲያኖችን ወይም መንፈሳዊ አስተማሪዎችን በቤታቸው እንግድነት አይቀበሉዋቸውም ነበር። በክርስቲያኖችም ላይ ስደት በጸናበት ጊዜ ከአንዱ ከተማ ወደ ሌላው ሲሸሹ እንደ ሚዳቋ እየታደኑ በባርነት ይሸጡ ነበር። ስለዚህ በዚያን ጊዜ የቤተ ክርስቲያን አባላትና አገልጋዮች እነዚህን ስደተኞች ተቀብለው ማስተናገድ ተግባራቸው ነበረ። መንፈሳዊ መሪዎች ክርስቲያኖችንም ሆነ ያላመኑ ሰዎችን ለማስተናገድ የተከፈተ በር እንዲኖራቸው ያስፈልጋል።

የከፍተኛ ድርጅት ባለቤትና በቤተ ክርስቲያን ውስጥ መልካም ተሳትፎ የነበረው አንድ የዚህ መጽሐፍ ጸሐፊ ጓደኛ ለችግረኞችና እርሱን ለመጠየቅ ለሚመጡ ሰዎች የተዘጋጀ ቤት ነበረው። ይህም ድርጊቱ ለሕይወቱ ጥሩ ነበረ፤ ለቤተ ክርስቲያንም መልካም ከመሆኑም በላይ ታማኝ አገልግሎቱን እንቃቅቶለታል፥ በሕይወቱም በልጽጓል፥ ሌሎችም ተባርከውበታል።

ሰውን ከአገልጋይነት ወደኋላ የሚያስቀሩት ነገሮች ምኞትና የገንዘብ ፍቅር ናቸው። ታማኝ አገልጋይ ከሰዎች በሚያገኘው የእጅ መንሻ ስጦታ ወይም የገንዘብ ኃይል ምክንያት ከትክክለኛው አቋሙ መዋዠቅ አይኖርበትም። የአገልግሎቱንም መስከ ሲገመግም ከርሱ የሚያገኘውን ደመወዝ አይመለከትም፤ ከፍም ዝቅም ቢል ለርሱ ምንም አይደለም።

ጆን ወስሊ ያንድ ሰባኪን አገልግሎት ሲያስታውስ እንዲህ ብሏል፡- «በቅን አስተሳሰብ እርሱን የሚመስል ሰው በአውሮፓም ሆነ በአሜሪካ አግኝቼ አላውቅም። ብዙ ዓመታት ወዳገለገለበት ሰበካ ሳይዛወር በፊት አሠሪው ላንተ ጥሩ ሰበካ አግኝቻለሁ፥ ሰበካው ሰፊ አይደለም፥ ሥራው ቀለል ያለ ነው፥ የወር ደመወዙ በጣም ብዙ ነው፥ ያገሩም አቀማመጥ ለጤና አመቺ ነው ቢለው፥ ደመወዙ በዝቷል፥ ሥራው ግን አንሷል። ስለዚህ ይህ ሰበካ ለኔ የሚሆን አይደለም» በማለት አገልጋዩ መልስ ሰጥቶታል። አሠሪውም፡- አብዛኛዎቹ አገልጋዮች እንዲህ ያለ መልስ አይሰጡም፤ እዝናለሁ። ሌላ ተመሳሳይ ሰበካ መቼ እንደማገኝልህ አላውቅም። ለመሆኑ ማድሌ በተባለው ሰበካ ልታገለግል ትፈቅዳለህ? ብሎ መልሶ ቢጠይቀው አዎን የኔ ወንድም! ይህ ልክ ለኔ የተዘጋጀ ሰበካ ነው ሲል መልስ ሰጥቶታል። ዓላማዬ ላንተ አመቺ ሰበካ ማግኘት ነበር፤ ነገር ግን አንተ አልፈልግም ባይ ከሆንህ ይህ ሰበካ ከማድሌ ይልቅ እጥፉን ደመወዝ ስለሚያስገኝ አገልጋይ አላጣም ብሎ በማድሌ እንዲያገለግል ፈቅዶለታል።»

ሰውን ያልተመኘውና የገንዘብ ፍቅር ያልገዛው ይህ አገልጋይ እቻ ያልተገኘለት አገልግሎት ከማቅረቡም በላይ በጽሑፍ የሰፈረው የሕይወት ታሪኩ ብዙ አንባቢያንን ባርኳል።

## ታማኝ አገልጋይ በቤተሰቡ ውስጥ
## የሚኖረውን ሁኔታ የሚመለከቱ መመዘኛዎች

በትዳር ዓለም ውስጥ የሚገኝ ታማኝ አገልጋይ ቤተሰቡን በእግዚአብሔር ፈቃድ በመምራት የመሪነት ችሎታ ያለው መሆኑን ማሳየት አለበት። «ልጆቹን በጭምትነት ሁሉ እየገዛ የራሱን ቤት በመልካም የሚያስተዳድር» ሊሆን ይገባዋል። ብዙ መንፈሳዊ መሪዎችና ሚስዮናውያን ቤተሰባቸውን የማስተዳደሩ ነገር ስላልሰመረላቸው ታላቁ መንፈሳዊ ሥራቸው ውድቅ የሆነ ይመስላል።

እንግዲህ ይህን ነገር አሟልቶ ለመገኘትና ሰውዬው በቤተሰብ አስተዳደር በኩል ያለውን ሸክም ለመወጣት እንዲችል ሚስቱም የሥራው ተባባሪ ለመሆን ራስዋን መሥዋዕት አድርጋ ለማቅረብ ፈቃደኛ መሆን ይገባታል። ብዙ ያስተዳደር ተሰጥዎ ያላቸው ሰዎች ከሚስቶቻቸው ሕይወት ሸካራነት የተነሣ ከፍተኛ መንፈሳዊ ደረጃቸውንና ኃይላቸውን አጥተዋል። መንፈሳዊ አገልጋይ የራሱን ቤተሰብ በእግዚአብሔር ቃል መሠረት በአግባብና በትክክል መምራት ካልቻለ የእግዚአብሔርን ቤተሰብ በተቃናና እግዚአብሔር በሚወደው መንገድ እንዴት ሊመራ ይቻለዋል? የገዛ ቤቱን በአግባብ የማይመራ፥ ልጆቹ ከቁጥጥር ውጭ ሆነው ጋጠወጥና መረን

ከሆኑ፣ ሌላውን ቤተሰብ በፍቅር ለመሳብና ለመቀበል ያለው ኃይል እየደከመ በመሄዱ በመጨረሻ ከነጭራሹ ይጠፋል።

መንፈሳዊ አገልጋይ ለቀሩት ሰዎች ጥቅምና ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት መሳካት የሚሯሯጥ ከሆነ የገዛ ራሱን ቤተሰብ ችላ ሊልና እንደ ቀላል ነገር ሊቆጥር እንዲሁም ያለበትን የቤተሰብ ኃላፊነት ቀላል አድርጎ ሊመለከት አይገባውም። በእግዚአብሔር አሠራር እርሱ የሰጠንን ተግባር ወይም ኃላፊነት ለመወጣት የምናደርገው ጥረት ሌላውን ኃላፊነት ችል እንድንል አያደርገንም። ማንኛውንም ዓይነት ተግባር መወጣት የሚቻልበት ጊዜ አለ። አንድ ሰው መንፈሳዊ ኃላፊነት ተሰምቶት ሌሎችም እንዲተባበሩት በፍቅር መምራት የሚችል ሰው መሆኑ የሚታወቀው ቤተሰቡን በፍቅርና በመልካም መግባባት መምራት በመቻሉ ነው። ብዙ ሰዎች ቤተሰባቸውን መምራት ባለመቻላቸው ታማኝ አገልጋዮች መሆን ሳይችሉ ቀርተዋል።

## የመንፈሳዊ ሕይወት ብስለት መመዘኛዎች

መንፈሳዊ ብስለት ለመንፈሳዊ አገልጋይነት እጅግ በጣም የሚያስፈልግ ነገር ነው። አዲስ አማኝን በአገልግሎት ማሰማራት ጨርሶ አያስፈልግም። «አዲስ» የሚለው ቃል የሚያመለክተው በቅርብ ጊዜ ያመነውን ሰው ነው። አንድ ተክል ሥር ሰዶ እስከሚያድግ ድረስ ጊዜ ይወስድበታል። ዕድገቱም ሊፋጠን አይችልም። ፍሬ ከማፍራቱ በፊት ወደ ታች ሥር መስደድ ይኖርበታል። ቤንጌል የተባለው ምሁር ቃሉን ሲተነትን እንዲህ ብሏል፡- «አዲስ አማኞች ብዙ እንቅስቃሴ አላቸው፤ ነገር ግን የቀራንዮ መስቀል መንገድ በመራመድ ብዙ ልምምድ የላቸውም።» በ1ጢሞ.3፡10 ደግሞ ጳውሎስ፣ ዲያቆን ሊሆን የሚገባው ምን ዓይነት ሰው እንደሆነ ሲገልጽ «እነለው ኃይል እየደከመ በመሄዱ በመጨረሻ ከነጭራሹ ይጠፋል።

መንፈሳዊ አገልጋይ ለቀሩት ሰዎች ጥቅምና ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት መሳካት የሚሯሯጥ ከሆነ የገዛ ራሱን ቤተሰብ ችላ ሊልና እንደ ቀላል ነገር ሊቆጥር እንዲሁም ያለበትን የቤተሰብ ኃላፊነት ቀላል አድርጎ ሊመለከት አይገባውም። በእግዚአብሔር አሠራር እርሱ የሰጠንን ተግባር ወይም ኃላፊነት ለመወጣት የምናደርገው ጥረት ሌላውን ኃላፊነት ችል እንድንል አያደርገንም። ማንኛውንም ዓይነት ተግባር መወጣት የሚቻልበት ጊዜ አለ። አንድ ሰው መንፈሳዊ ኃላፊነት ተሰምቶት ሌሎችም እንዲተባበሩት በፍቅር መምራት የሚችል ሰው መሆኑ የሚታወቀው ቤተሰቡን በፍቅርና በመልካም መግባባት መምራት በመቻሉ ነው። ብዙ ሰዎች ቤተሰባቸውን መምራት ባለመቻላቸው ታማኝ አገልጋዮች መሆን ሳይችሉ ቀርተዋል።

## የመንፈሳዊ ሕይወት ብስለት መመዘኛዎች

መንፈሳዊ ብስለት ለመንፈሳዊ አገልጋይነት እጅግ በጣም የሚያስፈልግ ነገር ነላቸውን፣ በአመለካከታቸው መንፈሳዊ የሆኑትንና ለሹመትም ጉጉት የሌላቸውን ሰዎች ለመምረጥ ጥንቃቄ መደረግ አለበት።

ጳውሎስ ይህ ዓይነቱ ጥንቃቄ የተሞላበት ምርጫ አስፈላጊ እንዲሆን ያደረገበት ምክንያት «በትዕቢት ተነፍቶ በዲያብሎስ ፍርድ እንዳይወድቅ» በማለት ገልጾታል። አዲስ ክርስቲያኖች በመንፈሳዊ ሕይወታቸው ስላልጎለመሱና ገና ሥር ሰደው ስላልጸኑ ለመንፈሳዊ አገልጋይነት ብቁ አይሆኑም። ስለዚህ በመንፈሳዊ ሕይወት ላልበሰሉ ሰዎች ቁልፍ የሆኑትን አገልግሎቶች

ያለውን የእግዚአብሔርን መንጋ ጠብቁ፤ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ በውድ እንጂ በግድ ሳይሆን፤ በበጎ ፈቃድ እንጂ መጥፎውን ረብ በመመኘት ሳይሆን ጎብኙት፤ ለመንጋው ምሳሌ ሁኑ እንጂ ማኅበራችሁን በኃይል አትግዙ፤ የእረኞችም አለቃ በሚገለጥበት ጊዜ የማያልፈውን የክብርን አክሊል ትቀበላላችሁ። እንዲሁም ጎበዞች ሆይ ለሽማግሌዎች ተገዙ፤ ሁላችሁም እርስ በእርሳችሁ እየተዋረዳችሁ ትሕትናን እንደ ልብስ ታጠቁ፤ እግዚአብሔር ትዕቢተኞችን ይቃወማልና ለትሑታን ግን ጸጋውን ይሰጣል።

እንግዲህ በጊዜው ከፍ እንዲያደርጋችሁ ከኃይለኛው ከእግዚአብሔር እጅ በታች ራሳችሁን አዋርዱ፤ እርሱ ስለ እናንተ ያስባልና የሚያስጨንቃችሁን ሁሉ በእርሱ ላይ ጣሉት» 1ጴጥ.5፡1-7።

ጴጥሮስ በተፈጥሮው የአገልጋይነት ችሎታ የነበረውና ተቀባይነትን ማግኘት የቻለ ሐዋርያ ነበር። ጴጥሮስ ያደረገውን ሌሎቹም ሐዋርያት ያደርጉ ነበር። ጴጥሮስ ወደ ሄደበት ሌሎቹም ይሄዱ ነበር። ጴጥሮስ «ዓሣ ለማጥመድ መሄዴ ነው» አለ። ሌሎቹም «እኛም ከአንተ ጋር እንሄዳለን» ብለው አጅበውት ሄዱ። ጴጥሮስ መሪ በነበረበት ወቅት በችኩልነቱ ያበላሻቸው ነገሮች ጥቂት አይደሉም። ቢሆንም በአገልግሎቱ ላይ ሃሳብ ጽኑና የማያወላውል ስለነበረ ሌሎቹን የመሳብና የመምራት ችሎታ ነበረው። ስለዚህም ከደካማ ጎኑ ይልቅ ትጋቱ እጅግ ጎልቶና በልጦ ይታይ ነበር። በዚሁ መልእክቱ ውስጥ መንፈሳዊ መሪዎች ለሆኑ ሰዎች የሰጠው ማሳሰቢያ በመንፈሳዊ ሕይወቱ በጎለመሰበት ወቅት ከልምምድ ያገኘው መሠረታዊ ምክር እንደሆነ እንረዳለን። ቀላልና ትክክለኛ ነው ብሎ ባሰበው ዘይቤ ለማንኛውም ዘመን መንፈሳዊ አገልጋይ ይጠቅማል ብሎ የገመተውን ትምህርት አቀነባብሮ አቅርቧል።

በጎችን በማገድ የብዙ ጊዜ ልምምድ ያለው ሰው በእርሱ ኃላፊነት ሥር የሚጠበቁትን በጎች እንዴት አድርጎ በእንክብካቤ መያዝ እንደሚገባው ያውቃል። «አንተም ደግሞ ልትጠብቃቸውና ልትመግባቸው በእጅህ አደራ የተሰጡህን የእግዚአብሔርን ሕዝቦች በሚገባ ጥንቃቄ ወስደህላቸው እንደሆነ ተመልከት» 1ጴጥ.5፡2። ይህ ጥቅስ ጴጥሮስ ጌታን ከካደ በኋላ ከታላቁ እረኛ ከኢየሱስ ጋር ያደረገውን መጠይቅ ያንጸባርቃል፤ በተጨማሪ ዮሐ.21፡15-17 ተመልከቱ። ይህም የቀድሞ ልምምዱን የሚያስታውስ ይመስላል። የደብዳቤው ተቀባዮች ማለት የተበተኑት መጻተኞች ያለባቸውን ስደት ከግል ልምምዱ ያውቃል፤ ስለዚህም የእረኛ እንክብካቤና መጽናናት የበለጠ እንደሚያስፈልጋቸው ያውቃል። ለሽማግሌዎችም የጻፈላቸው ይህንን በማሰብ ነው።

በዚህ ላይ ማስተዋል የሚገባን ጴጥሮስ ይህንን ደብዳቤ ለቤተ ክርስቲያኒቱ ሽማግሌዎች የጻፈላቸው ራሱን እንደ ተቆጣጣሪ በመቁጠር ሳይሆን ከሽማግሌዎቹ እንደ አንዱ አድርጎ በማቅረብና በሽማግሌዎች ላይ ያለው ኃላፊነት በእርሱም ላይ እንዳለ አድርጎ በመግለጽ ነው። መልእክቱን ያስተላለፈላቸው በበላይነት ሥልጣን አልነበረም፤ ራሱን ከእነርሱ ጋር አንድ እንደሆነ በመቁጠር ነበር። ይህም መሪነትን ለመለማመድ ጥሩ መሠረት ነው። ልክ ከእርሱ ጋር እኩል እንደሆኑ አድርጎ ቆጥሯቸዋል። ከውድቀቱ የተነሣ የተቀጣና በቀራንዮም ፍቅር ልቡ የተደቆሰበት ሰው መሆኑን ያሳያቸዋል። የእረኛ ልብ የሌለው ሰው የእረኛን ሥራ መሥራት አይችልም።

ጴጥሮስ የመሪዎችን ልብ በማነሣሣት ይጀምራል። መንፈሳዊ አገልጋይ የሆነ ሰው የተቀበለውን ኃላፊነት መወጣት ያለበት ኃላፊነቱን እንደ ግዳጅና እንደ ዕዳ በመቁጠር

አይደለም፤ በፈቃደኝነት እንጂ ልወጣው የማልችለው ዕዳ ነው በሚል መንፈስ ሊሠራ አይገባውም። ጴጥሮስ ይህንን መልእክት በጻፈላቸው ጊዜ የነበረው የአካባቢው ሁኔታ እጅግ የጠበቀና የሚያስፈራ ቢሆንም የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች እንደዚህ ባለ ሁኔታ ውስጥ ልባቸው ተደናግጦ አንድ እርምጃ እንኳ ወደኋላ ዝንፍ እንዳይሉ ይመክራቸዋል። ከዚህም ጋር በማያያዝ ከመለኮታዊ ፍቅር የተነሣ ሥራቸውን በይበልጥ እንዲያከናውኑ እንጂ ሃሳባቸው ተበታትኖ የግብር ይውጣ ሥራ በመሥራት እንዳይባክኑ ያሳስባቸዋል።

ይህ የመጋቢነት ተግባር እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ በግብር ሊገለጥና በተግባር ሊፈጸምስም ይገባዋል እንጂ እንደ እነርሱ ፈቃድ የሚከናወን እንዳልሆነ ያሳስባቸዋል።

ስለዚህ ጴጥሮስ ሽማግሌዎችን «በእናንተ ዘንድ ያለውን የእግዚአብሔርን መንጋ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ጠብቁት» ይላቸዋል። እስራኤላውያን ለእግዚአብሔር የተለየ ሕዝብ እንደሆኑ ሁሉ በየትኛውም ሥፍራ የምናገለግላቸው ሰዎች በእግዚአብሔር ኃይል ተለይተው ለኛ የተሰጡ ናቸው። ስለዚህ ለእነርሱ ያለንን አስተያየት እንደ እግዚአብሔር አስተሳሰብ ቅንና በጎነት የተሞላው ሊሆን ይገባዋል። እኛም እንደ እግዚአብሔር ልብ በፍቅር ልንጠብቃቸው ይገባናል። ስለዚህ የእግዚአብሔርን ፍቅርና ይቅርታ እንዲሁም ወሰን የሌለውን የትዕግሥቱን አገልግሎት ለሰዎች ለማሳየት ምን ያህል ብሩህ የሆነ መገለጥ! ምን ዓይነት የልብ ፍላጎት ሊኖረን ይገባ ይሆን!

እግዚአብሔር ለሚጠራን አገልግሎት እምቢ ማለት አይገባም። ምክንያቱም ሥራውን ማከናወን የምንችለው በእኛ ታዋቂነትና ብቁነት ሳይሆን እርሱ በሚሰጠን ኃይልና ብርታት ነው። ይሄን አገልግሎት በራሱ ችሎታ እንደ እግዚአብሔር ፍላጎት አድርጎ ማከናወን የሚችል ማን ነው? ሙሴ ብቁ አለመሆኑን ለማሳየት ድካሙን ከተለያየ አንጻር ባመለከተበት ወቅት የእግዚአብሔር ቁጣ ነደደበት፤ ዘጸ.4፡14።

መንፈሳዊ አገልጋይ ከአገልግሎቱ የሚያገኘውን ጥቅምና ትርፍ ፈጽሞ መመልከት አይገባውም። «ሥራህን በምትሠራበት ጊዜ ትጋትህ ከሥራው አንጻር በምታገኘው ጥቅም ላይ የተመሠረተ አይሁን። አሳፋሪ ለሆነ ጥቅምም አትገዛ።» ይህን በማለቱ ጴጥሮስ የስግብግብነት ባሕርይ በሥራ ጓደኛው በይሁዳ ላይ ምን ያህል ኃይል እንደነበረው ያስታውሳል። ስለዚህ እነዚህ የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች ይህንን ከመሰለው ምኞት ጨርሶ የነጹ እንዲሆኑ ይመኝላቸዋል። መንፈሳዊ አገልጋይ ሥራውን በሚያከናውንበት ጊዜ በሚያገኘው ጥቅም ላይ ልቡ የተመሠረተ መሆን የለበትም። ምዕመናን አገልጋዩ ጥቅም ፈላጊ አለመሆኑን ከተረዱ የሚናገራቸውን ቃል ይበልጥ ያዳምጣሉ።

ራስ ወዳድነት ተብሎ የተተረጎመው የግሪክ ቃል የሚያመለክተው የገንዘብን ፍቅር ብቻ አይደለም፤ ምስጋናን ዝናንና ከንቱ ውዳሴን መፈለግ ራስ ወዳድነት ጭምር ነው፤ ይህም ከፍተኛ ጥፋት የሚያስከትል ፈተና ነው። ሰዎች ከገንዘብ ይልቅ በሕዝብ ዘንድ ታዋቂነትንና ሥልጣንን ማግኘት ይመኛሉ።

«አስጸያፊ የሆነው ጠባይ የገንዘብ ሱሰኝነት ወይም ዝነኛነት ይሁን ለይቶ ማወቅ ያስቸግራል» ሲሉ አንድ የእግዚአብሔር ሰው ተናግረው ነበር። አንድ ሰባኪ በሕዝብ ዘንድ ተወዳጅ ለመሆን ድምጹን አሳምሮ ስብከቱንም አለስልሶ ሊቀርብ ይችል ይሆናል፤ ሌሎችም ክርስቲያን ሠራተኞች እንደዚሁ ስማቸውን ለማስጠራት ይፍጨረጨሩ ይሆናል፤ ስብከቶቻቸውንም ያሰራጩ ይሆናል፤ ሞገስንም ሊያተርፉ ይችሉ ይሆናል፤ ሆኖም ይህ ሁሉ

ለአገልግሎታቸው የማይበቁ ሊያደርጋቸው ይችላል። ለበጎቹም የማያስፈልገው ነገር ምን እንደሆነ እንዳያዩ አይኖቻቸውን ሊያሳውር ይችላል።

ክርስቲያን አገልጋይ ከእኔ በቀር ማንም ተሰሚነት ማግኘት የለበትም የሚል አምባገነን ሊሆን አይገባውም። «ማኅበሮቻችሁን በኃይል አትግዙ!» 1ጴጥ.5፡3። ዝነኛና ታላቅ ሰው ለመባል የሚጓጓ መንፈሳዊ አገልጋይ ብዙ ሳይቆይ በመንጋው ላይ መኩራራት ይጀምራል። ጥቂት ሥልጣን መልካም አረማመድን በኩራት ሞልቶ ሊያበላሽ ይችላል። ራሱን ዝቅ ያደረገ የእግዚአብሔር አገልጋይ ይህንን ዓይነት ጠባይ ከልቡ ማስወገድ አለበት።

እርሱም በመንጋው ፊት መልካምና ቅን አርአያነቱን ማሳየት ይኖርበታል። «ለመንጋው ምሳሌ ሁኑ» 1ጴጥ.5፡3። ጳውሎስ ጢሞቴዎስን በመምከር የጻፈለት ደብዳቤ «በቃልና በኑሮ፥ በፍቅርም በእምነትም በንጽሕናም ለሚያምኑቱ ሁሉ ምሳሌ ሁን» ይላል! 1ጢሞ.4፡12። ጴጥሮስም ለቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች ሲጽፍ በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ የሚያሳዩት የአገልግሎት መንፈስ ለሌሎቹ ጥሩ ምሳሌነት ያለው እንዲሆን ይመክራቸዋል። መግቡ የሚለው ትእዛዝ የመጋቢን ሥራ ያመለክታል። እረኞች በሥልጣናቸው ተመክተው እንዳይባልጉ መንጎቹ የእግዚአብሔር እንጂ የእነርሱ እንዳልሆኑ መገንዘብ አለባቸው! ስለ ሰጡትም አገልግሎት የእረኞች አለቃ ለሆነው ለጌታ መልስ እንደሚሰጡ መረዳት አለባቸው። እርሱ የእረኞች አለቃ ነው! እነርሱ ደግሞ ከእርሱ በታች ሆነው መንጋውን የሚያሰማሩ የበታች ጠባቂዎችና መጋቢዎች ናቸው።

በእግዚአብሔር ቃል መሠረት የእረኞች አገልግሎት ስለ በጎች በእግዚአብሔር ፊት መጸለይንና መማለድንም ያጠቃልላል። አንድ የሕንድ ተወላጅ የሆኑ መንፈሳዊ አገልጋይ በሀገራቸው ለሚገኙ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ዕለት ዕለት አንድ በአንድስማቸውን በመጥቀስ ይጸልዩላቸው እንደነበረ ይነገራል። እኚህም ሰው በሰላሳ ዓመት የአስተዳደር ልምምዳቸው የአባሎች ቁጥር በሦስት እጥፍ ከማደጉም በላይ በመንፈሳዊ አገልግሎታቸው በጣም ፍሬያማ ሆነዋል።

መንፈሳዊ አገልጋይ ትሕትናን እንደ መቀነት መታጠቅ አለበት። መታጠቅ የሚለው የግሪክ ቃል ከነጭ መጎናጸፊያ ጋር ወይም አንድ አገልጋይ ሥራ ሲሠራ ከሚለብሰው ጨርቅ ጋር የተያያዘ ነው። መንፈሳዊ አገልጋይ የአገልጋይን ልብስ ለብሶ ለአገልግሎት መታጠቅ አለበት። ጴጥሮስ ይህን ሲል ጌታ ትሕትናን ሊያስተምራቸው የደቀ መዛሙርቱን እግር ለማጠብ ተነሥቶ በነበረበት ወቅት እኔ እንጂ አንተ ልታጥበኝ አይገባም ብሎ እምቢ ያለበትን ምሽት ሳያስታውስ አልቀረም። ጴጥሮስ ሽማግሌዎችን ይህን ከመሰለ አሳዛኝ ሁኔታ ሊጠብቃቸው ይወዳል። ብዙ ጊዜ በሥልጣን ውስጥ ትዕቢት ተሰውሮ የተቀመጠ ነገር ቢሆንም እግዚአብሔር ትዕቢተኛ ሰዎችን በአገልግሎቱ ውስጥ እንዲሰማሩ አይጋብዛቸውም። ይልቁን ከዚያ እንዲወገዱ ያደርጋቸዋል። ነገር ግን በእረኛነት ደረጃ የሚገኝ ሰው የዋህና ልበ ትሑት በሚሆንበት ጊዜ ጸጋ በጸጋ ላይ እየበዛለት ይሄዳል። ጴጥሮስ በ5ኛው ቁጥር ላይ መንፈሳዊ አገልጋዮች ምዕመናንን በየዋህነት መንፈስና በትሕትና እንዲቀርቡ ይመክራል። በቁጥር 6 ላይ ደግሞ ከኃይለኛው ከእግዚአብሔር እጅ በታች ራሳቸውን እንዲያዋርዱና ዝቅ ዝቅ እንዲያደርጉ ያሳስባቸዋል! «ስለዚህ ከኃይለኛው ከእግዚአብሔር እጅ በታች ራሳችሁን አዋርዱ» ይላቸዋል። ለአባባሉ «ራስን በትሕትና መንገድ አቅርብ» የሚል ትርጉም ልንሰጠው እንችላለን! ይህም ትክክለኛ ሃሳቡን ይሰጠናል። ጴጥሮስ «የእረኞች አለቃ በሚገለጥበት ጊዜ የማያልፈውን የክብር አክሊል ትቀበላላችሁ» በማለት ለከፍተኛ አገልግሎት የሚያነሣሣ ሌላ

ቀስቃሽ ሃሳብ ያቀርባል፤ 1ጴጥ.5፡4። በዚህ ሥፍራ «የማያልፍ» የሚለው ቃል የማይጠወልግ ማለት ነው። በግሪክ ማራቶን አሸናፊ ለሆነው ሰው ይሰጥ የነበረው ጉንጉን የቅጠል አክሊል ወዲያው ይጠወልግ ነበር፤ ጌታ ሲመጣ ለታማኝ አገልጋይ የሚሰጠው ሽልማት ግን ዘወትር የሚያሸበርቅ ነው።

የእረኞቹ አለቃ የበታቹ እረኛ የራሱን ሸክም ለብቻው እንዲሸከም ስለማይተወው የተመቻቸ ሁኔታ ሊፈጥርለት ይችላል። በ1ጴጥ.5፡7 የእግዚአብሔር ቃል «እርሱ ስለ እናንተ ያስባልና የሚያስጨንቃችሁን ሁሉ በእርሱ ላይ ጣሉት» ስለሚል የበታቹ እረኛ ጭንቀቱን ማስተላለፍ ሊለማመድ ይችላል። ይህ ጴጥሮስ የጠቀመው ጭንቀት በተዘዋዋሪ መንገድ ከታማኝ አገልግሎት ጋር የሚያያዝ ነው። ጭንቀት የሚለው ቃል «ከስሜቶች ግጭት የተነሣ የተፈጠረውን የአዕምሮና የአስተሳሰብ ብልሽትን ያመለክታል።» በሥሩ ያለውን የእግዚአብሔርን መንጋ መጠበቅ ከመጠን በላይ ከባድ ይሆንብኛል ብሎ የበታቹ እረኛ መፍራት የለበትም። የሚከብዱትን መንፈሳዊ ችግሮች ጥንቃቄ ማድረግ በሚችለው በእግዚአብሔር ትከሻ ላይ በፈቃደኝነት ሊያሳርፍ ይችላል።

# ምዕራፍ 7

## ለመንፈሳዊ አገልግሎት አስፈላጊ የሆኑ ባሕርያት

«እንግዲህ ኤጲስ ቆጶስ እንዲህ ሊሆን ይገባል...» 1ጢሞ.3፡2፤ እግዚአብሔር አንድን ሰው ለመንፈሳዊ አገልግሎት ሲያዘጋጅ ምንጊዜም ያንን ሰው ሊያሰማራበት ያቀደው የአገልግሎት መስክ አለው። ስለዚህ ሠራተኛውን ለሥራው ሊያዘጋጀው ስለሚችል አገልጋዩ ተልዕኮውን ለመፈፀም ብቃት እንዲኖረው የተፈጥሮና የፀጋ ስጦታዎች ይሰጠዋል። ጳውሎስ ግሩም የሆኑ መገልገያዎች ባይኖሩትና ልዩ ሥልጠና ባይደረግለት ኖሮ በአጭር የሕይወት ዘመኑ ውስጥ ይህንን የመሰሉ አስደናቂ ውጤቶች አይገኙፀፍም ነበር።

አዶኒራም ጃድሰን ሥራውን በበርማ እንዲጀምር እግዚአብሔር አስፈላጊ የሆኑትን ባሕርያት ማለት ከትሕትና ጋር የተዋሐደ በራስ መተማመን፥ አስተዋይነት የተሞላው ኃይል፥ ትዕግሥት፥ ራስን መካድ እንዲሁም ድፍረትና ለነፍሳት መራራት በመስጠት አዘጋጅቶታል። ታላቁ የቤተ ክርስቲያን መሪ ማርቲን ሉተር ሰዎች በቀላሉ ሊቀርቡት የሚችሉት፥ ከንቱነት ያልታየበት፥ ቀላል ኑሮ የኖረ፥ ባለ ብርቱ ስሜት፥ በደስታና በፈገግታ የተሞላ፥ በዘመኑ ታማኝ፥ ፍፁምና እውነተኛ ሰው እንደነበር ተነግሮለታል። በተጨማሪም የማይናጋ ድፍረት፥ የማያወላውል ጽኑ እምነትና የክርስቶስ ፍቅር ነበረው። ስለዚህ ያፈራቸው ሰዎች በገመድ የታሠሩ ይመስል ከእርሱ ጋር መጣበቃቸው እንዲሁ አልነበረም ለካ!

ፕሮፌሰር ጂ. ዋርከ ሃድሰን ቴይለር ሥራውን በቻይና እንዲጀምር እግዚአብሔር አስፈላጊ በሆኑት ነገሮች እንዴት እንዳስታጠቀው በሚያሳይ መንገድ እንዲህ ሲል ገልፆታል፦ «በእምነትና በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ፥ ራሱን ለእግዚአብሔርና ለጥሪው ያስረከበ፥ ፍፁም ራሱን የካደ፥ ከልብ የመነጨ ርኅራኄ፥ ብርቱ የጸሎት ኃይል፥ አስደናቂ የማስተባበር ችሎታ፥

የማይዝል ታታሪነት የነበረውና እንዲሁም አስገራሚ ሰዎችን የሚስብና እንዲቀርቡት የሚማርክ ባሕርይ የነበረው ሰው ነበር።

ከዚህ በላይ የተመለከትናቸው ሰዎች ሁሉ በስተኋላ ለተጠሩላቸው ልዩ አገልግሎቶች ብቁ የሚያደርጓቸው ስጦታዎች ተሰጥተዋቸው ነበር። ሆኖም በዘመናቸው ይኖሩ ከነበሩት ሰዎች እንዲልቁ ያደረጋቸው እነዚህን ስጦታዎችና ፀጋዎች መስዋዕትነት በመክፈልና ራሳቸውን በመግዛት ስላበለፀጓቸው ነበር።

እምነት የሚጣልበት አገልጋይ ለማግኘት ተኮትኩተው ማደግ የሚገባቸውን አንዳንድ ባሕርያት ቀጥለን እንመለከታቸዋለን።

## ድፍረት

ለመንፈሳዊ አገልጋይ ከሚያስፈልጉት ነገሮች አንዱ እግዚአብሔርን በመፍራት ላይ የተመረኮዘ ድፍረት ነው፤ አገልጋይ ዘወትር ሥነ ምግባራዊ ድፍረት ያስፈልገዋል። አንዳንድ ጊዜም ከሥራ አንፃር ልበ ሙሉ መሆን ያሻዋል። ድፍረት ማለት ሰዎች አደገኛ ሁኔታን ወይም ችግርን ያለ ፍርሃት እንዲጋፈጡ የሚያስችላቸው ኃይል ማለት ነው።

ማርቲን ሉተር እንዲህ ዓይነት ድፍረት ነበረው። እንደ እርሱ ፍርሃት የሌለው ሰው እንደማይገኝ ይነገርለታል። አንድ ጊዜ ዎርምስ ወደተባለ ቦታ ለመሄድ በጉዞ ላይ ሳለ «በእኔ ውስጥ የማይገኙት ነገሮች ፍርሃትና ወደኋላ ማፈግፈግ ብቻ ናቸው» በማለት ተናግሯል። ሉተር ከቤተ ክርስቲያን ባለሥልጣኖች ጋር የተከራከረበት ጉባዔ የተደረገው ዎርምስ በተባለው ከተማ ነበር። በዚህ ወቅት አንዳንዶች እርሱን ለመግደል አሲረው ነበር። አደገኛ ነገር ይገጥመዋል ብለው በማሰብ ሲያስጠነቅቁት የነበሩት ወዳጆቹ ከዓላማው እንዲያፈገፍግ የመምከር ሙከራ አድርገዋል። ሆኖም ሉተር አልተረታላቸውም። ወዳጆቹ ወደ ዎርምስ አትሂድ ብለው ቢመክሩትም ሉተር «በዎርምስ የሚገኙት አጋንንት በቆርቆሮ ከዳን በተሸፈነ ቤት ውስጥ እንዳሉት ምስማሮች ቢበዙም እንኳ ከመሄድ አልቆጠብም» ብሎ መልስ ሰጥቷቸዋል።

ሉተር ወደ ጀርመን ንጉሥ ፊት ቀርቦ እምነቱን እንዲለውጥ ተጠይቋል። የቀረበለትንም ጥያቄ የሚቀበለው ወይም የማይቀበለው መሆኑን በአንድ ቃል እንዲገልጽ ሲጠየቅ «መጽሐፍ ቅዱስ ይህንን እንዳደርግ ካልነገረኝ ወይም ሌሎች ግልጽ ምክንያቶችን ካላገኘሁ በስተቀር በፍጹም እምነቴን ልተው አልችልም» የሚል መልስ ሰጥቷቸዋል። በተጨማሪም «የሃይማኖት ጉባዔ ወይም ጳጳሱ ብዙ ጊዜ ስለሚሳሳቱ ይህንን ጉዳይ ለእነርሱ ልተውላቸው አልፈቅድም፤ ሕሊናዬ የእግዚአብሔር ቃል ተገዥ ነው» በማለት የልቡን ድፍረት ገልጦላቸዋል።

ሉተር ከያዘው እምነት ወደኋላ እንዲያፈገፍግ እንደገና ሌላ ዕድል ተሰጠው። በዚህም ጊዜ እጆቹን አጣጠፈና «ይኸውና አለሁላችሁ፤ ሌላ ምንም ላደርግ አልችልም። እግዚአብሔር ሆይ ዕርዳኝ» አለ። ከብዙ ዓመታት በኋላ ከመሞቱ ጥቂት ቀናት ቀደም ብሎ ይህንን ሁኔታ አስታወሰና «በዚያን ሰዓት ምንም አልፈራሁም ነበር፤ ይህን ዓይነት ድፍረት ሊሰጥ የሚችል እግዚአብሔር ብቻ ነው። አሁን ያተረፍኩትን ደስታ አገኛለሁ ብዬ አላሰብኩም ነበር» ብሎ ተናግሯል።

ሰዎች ሁሉ በተፈጥሯቸው እንዲህ ያለ ድፍረት አላቸው ማለት አይቻልም፤ ይህም እውነት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ግልጽና ተዘዋዋሪ በሆኑ መንገዶች ተገልጿል። በተፈጥሮው ምንም ፈሪ ቢሆን የፍርሃት ምርኮኛ አልሆንም ብሎ በእግዚአብሔር የሚጽናና ሰው ይህንን ዓይነት ድፍረት ሊጎናጸፍ ይችላል። እግዚአብሔር የመረጣቸው በተለያዩ ዘመናት የነበሩትና የሚኖሩት አገልጋዮች ምንም ልባቸው ቢፈራም ጥሩ ድፍረት ያላቸው ሰዎች እንዲሆኑ ትዕዛዝ ተሰጥቷቸዋል። እነርሱ ፍርሃት የሌለባቸው ሰዎች ቢሆኑ ኖሮ ትዕዛዙ አያስፈልግም ነበር። አገልጋይ ድፍረት ያለው ሰው የመሆን ኃላፊነት አለበት፤ ይኸውም በውስጡ የሚኖረው መንፈስ ቅዱስ ይህንን ማድረግ ስለሚያስችለው ነው።

እስኪ ዮሐ.20፡19ንና የሐዋ.4፡13ን እናነጻጽር። ዮሐ.20፡19 «ደቀ መዛሙርቱ ተሰብስበው በነበሩበት፥ አይሁድን ስለፈሩ ደጆቹ ተዘግተው ሳለ» ሲል የሐዋ.4፡13 ደግሞ «ጴጥሮስና ዮሐንስም በግልጽ እንደተናገሩ ባዩ ጊዜ» ይላል። ሁለቱ ድርጊቶች የተፈጸሙት በጥቂት ወራት ተራርቀው ነበር፤ በአይሁዶች ፊት የተለያዩ ሁኔታዎች የታየባቸው ደቀ መዛሙርት ግን እነዚያው ናቸው። ይህ ድፍረታቸው ከየት መጣ? መጽሐፍ ቅዱስ ለዚህ ጥያቄ «ሁሉም በመንፈስ ቅዱስ ተሞልተው ነበር» የሚል መልስ ይሰጣል። መንፈስ ቅዱስ የሰውን ሁለንተና በቁጥጥሩ ሥር በሚያደርግበት ጊዜ የፍርሃት መንፈስ ሳይሆን የኃይል መንፈስ ይሰጠዋል፤ 2ጢሞ.1፡7።

አንድ አገልጋይ ደስ የማያሰኙና በጥፋት የተሞሉ ሁኔታዎች ቢገጥሙት አይሸበርም፤ እንዲሁም እነዚህ ነገሮች በሰዎች ዘንድ ያለውን ግምት እንዲያጣና እንዲጠላ የሚያደርጉት ቢሆኑም እንኳ አይበግሩትም። ሁኔታዎቹን በሚመለከት በረጋ መንፈስ ተገቢውን ውሳኔ ሊያስተላልፍ ይፈቅዳል። የሰዎች ተቃውሞና ግትርነት አያስበረግገውም። ድፍረት አልፎ አልፎ በግልጽ የማይታይ ሊሆን ይችላል፤ ሆኖም ሥራው ሙሉ በሙሉ ተሠርቶ እስኪያልቅ ድረስ ድፍረቱ መቀጠል ይኖርበታል።

ክርስቲያን አገልጋዮች በሁከት ውስጥ ድፍረትና እርጋታ ያላቸው ናቸው። ብጥብጥ በበዛበት ወቅትና ድክመቶች በሚታዩበት ሁኔታ ውስጥ ተከታዮቻቸውን ያበረታታሉ። ሌሎች የሚያደርጉትን ቢያጡና ግራ ቢጋቡም አገልጋዮች ግን እንዲህ አይሆኑም።

የሰናክሬም ሠራዊት ሲገጥመው ሕዝቅያስ በተረጋጋ መንፈስ ወታደሮቹን አዘጋጅቷል፤ ከዚያም ሕዝቡን ማጠናከር ጀምሯል። «ጽኑ አይዟችሁ፤ ከእኛም ጋር ያለው ከእርሱ ጋር ካለው ይበልጣልና ከአሦር ንጉሥና ከእርሱ ጋር ካለው ጭፍራ ሁሉ አትፍሩ፤ አትደንግጡም። ከእርሱ ጋር የሥጋ ክንድ ነው፤ ከእኛ ጋር ያለው ግን የሚረዳንና የሚዋጋልን አምላካችን እግዚአብሔር ነው» ብሎ አጽናንቷቸዋል። ሕዝቡም ሕዝቅያስ በተናገራቸው ቃላት ተጽናንቷል፤ 2ዜና 32፡7-8። ድፍረት ማለት ይህ ነው።

## ትሕትና

በንግድና በሌላ አስተዳደር ዓለም ያሉ ሰዎች ትሕትና የሚመኙት ወይም የሚፈልጉት ነገር አይደለም። የንግድ ሰው የሚፈልገውና የሚመኘው መከበርንና በሕዝብ ዘንድ ታዋቂ መሆንን ነው። በእግዚአብሔር ዓይን ግን ከፍተኛ ዋጋ የሚያገኘው ትሕትና ነው። ክርስቶስ ለታማኝ አገልጋይነት የሰጠው ትርጉም እንደሚያሳየው አገልግሎት ራስን ማሳወቅ ሳይሆን ራስን መሰወር ነው። ወደፊት ለሚገጥማቸው ኃላፊነት ክርስቶስ ደቀ መዛሙርቱን ያሠለጥን

በነበረበት ወቅት እንደ አሕዛብ አለቆች ራሳቸውን ማሳወቅ ሳይሆን በትሕትና ማገልገል ያለባቸው መሆኑን አስተምሯቸዋል፤ ማቴ.20፡25-27። መንፈሳዊ አገልጋይ ታዋቂ ሹመትና የብዙ ሰዎችን ድጋፍ ሳይሆን መሥዋዕትነት የተሞላበት አገልግሎት የሚሰጥበትን የተሰወረውን መንገድ ይመርጣል፤ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ያስተማረውንም ይፈጽማል።

መጥምቁ ዮሐንስ አገልግሎቱን ሲጀምር ታላቅ ሰው መሆን ያስቻለው በዘመኑ የነበሩትን ክፉ ሰዎች በድፍረት፥ በብልሃትና ኃይለኛ ቃላት በመናገር የሰዎችን ልብ መንካቱ ነው ብሎ የሩቅ ተመልካች ግምት መስጠት ይችል ይሆናል። ከሴቶች ከተወለዱት ሰዎች ሁሉ ይልቅ እርሱን ታላቅ ሰው ያደረገው ምስጢር ግን ስለ ኢየሱስ «እርሱ ሊልቅ እኔ ግን ላንስ ያስፈልጋል» የሚል ማረጋገጫ መስጠቱ ነው፤ ዮሐ.3፡30። ይህ ጥቅስ የእርሱን መንፈሳዊ አቋም አጉልቶ ይገልጸዋል።

አንድ አገልጋይ በመንፈሳዊ ሕይወቱ እያደገ መሄድ እንዳለበት ሁሉ በትሕትናውም ማደግ አለበት። ጳውሎስ በየጊዜው የትሕትና ጸጋ እየተጨመረለት ይሄድ እንደነበረ መመልከት ጥሩ ትምህርት ይሰጣል። አገልግሎቱን በጀመረበት ወቅት ሕይወቱንና የተጸየፈውን የቀድሞውን ሥራ በማስመልከት «እኔ ከሐዋርያት ሁሉ የማንስ ነኝ» በማለት ተናግሯል፤ 1ቆሮ.15፡9። ከዚህ በኋላ ደግሞ «ከቅዱሳን ሁሉ የማንስ» ብሎ እንደተናገረ ከኤፌ.3፡8 እንመለከታለን። የሕይወት ዘመኑ መጨረሻ ቀርቦ ጌታን ለመገናኘት ተዘጋጅቶ በነበረበት ወቅት ደግሞ «ከኃጢአተኞችም ዋና እኔ ነኝ» በማለት በ1ጢሞ.1፡15 ተናግሯል።

አንድ ክርስቲያን ምሁር ስለ ትሕትና ሲጽፍ፡- «እያንዳንዱን ቀን በአካባቢያችን ያሉትን ሰዎች ድካም በመሸፈን፥ እየወደድናቸው እያበረታታናቸው፥ አብረናቸው እየተደሰትን፥ ሐዘናቸውን እየተካፈልን፥ ወዳጅነታቸውን እያከበርን፥ ክፋታቸውን ችል እያልን፥ የሚፈጽሙብንን ተንኮል ይቅር እያልንና የአገልጋዮች አገልጋይ በመሆን ሌሎች ሰዎች ለመሥራት የሚጸየፉትን ሥራ ለመሥራት ፈቃደኛ እየሆንን እያንዳንዱን ቀን በትሕትና እናሳልፍ» ብሏል።

ታላቁ ዶክተር የሚል መጠሪያ የተሰጠው አንድ ምሁር ደግሞ በማስታወሻው ውስጥ እንዲህ የሚል ቁምነገር ጽፎ ነበር፡- «በሰዎች ፊት ታላቅ ሆኜ ብታይ፥ እግዚአብሔር ደግሞ ያለ እርሱ ከንቱ መሆኔን እንድመለከት ይረዳኛል፤ በራሴ ዓይን ታናሽነቴን እንድመለከት ይረዳኛል። በእኔ ይጠቀማል። ከእኔ ችሎታ የተነሣ ሳይሆን እርሱ በእኔ ተጠቅሞ ሥራውን እንዲሠራ እመኛለሁ፤ ዛፎችን የቆረጠ መጥረቢያ ብዙ ዛፎችን ጥያለሁ ብሎ ሊፎክር አይችልም። መጥረቢያው በራሱ ምንም የማድረግ ችሎታ የለውም፤ የሚያገለግለውም ለዛፍ ቆራጩ ነው። መጥረቢያውን የሠራው እራሱ ነው፤ ስለት አውጥቶለታል፤ በዚያውም ይጠቀምበታል። ዛፍ ቆራጩ ቢወረውረው ጥቅም የሌለው ያልረባ ብረት ሆኖ ይወድቃል። ይህን ሐቅ እንዳልረሳ ጌታ ይርዳኝ።»

ዛሬ የቤተ ክርስቲያን አገልጋይ የሚሆን ሰው ትናንትና ትሕትናውን በደስተኝነትና በታማኝነት በመሥራት የገለጸ ሰው ሳይሆን አይቀርም። አንድ የቤተ ክርስቲያን መሪ፡- «በኛ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የማገኘው ትልቁ እንቅፋት የሰው ሁሉ አዛዥ ለመሆን መመኘት ነው። ሊያገለግል የሚፈልግ ሰው አጥቻለሁ። ምናልባት ይህ ገንቢ የሆነ ምኞት ሊሆን ይችላል፤ ነገር ግን እኔ ጥቅሙን አልተረዳሁም» በማለት ጽፏል።

# ክፍል ሁለት

# ለመንፈሳዊ አገልግሎት የሚያበቁ ባሕርያት

# ምዕራፍ 8

## የደስተኝነት ስሜት

«እንዲሁም ዲያቆናት... ሊሆኑ ይገባቸዋል!» 1ጢሞ.3፡8።

ሰው በእግዚአብሔር አምሳል የተፈጠረ እንደመሆኑ መጠን ያለው የተደሳችነት ስሜት ከእግዚአብሔር የተሰጠው ስጦታ ነው፤ ይህም ሊሟላለት የሚችለው በአምላክ ብቻ ነው። ነገር ግን ይህንን ባሕርይ ሊቆጣጠረው ይገባል። ደግሞም ሊኮተኩተውም የሚገባ ስጦታ ነው። ንጹሕና የተሟላ የሆነ ተደሳችነት በውጥረት ውስጥ ላለ ሰው መዝናናትን ይሰጠዋል፤ ደግሞ በችግር ውስጥ ላለ ሰው ከማንኛውም ነገር ይልቅ መፍትሔ ይሰጠዋል። በአንድ አገልጋይ ውስጥ ያለ የተደሳችነት ባሕርይ ለሚሠራውም ሥራ ሆነ ለግል ሕይወቱ በዋጋ ሊተመን የማይችል ጥቅም ይሰጣል።

ሳሙኤል ጆንሴን የተባለው ምሁር ምክሩን ሲለግሥ፡- «ሰው ለመብላት ሰዓት እንደሚወስን ሁሉ ለመደሰትም ጊዜ መለየት ያስፈልገዋል» በማለት ተናግሯል። ሌላ ምሁር ደግሞ «አዕምሯችንን መኮትኮት ብቻ ሳይሆን ደስታ ልናገኝ የምንችልበትንም መንገድ መፍጠር አለብን» ብሏል። አንዲት ጸሐፊ፡- «በዚህ ዓለም ውስጥ ከመልካም ጸባያት ቀጥሎ ሊኖረን የሚገባ ነገር ተደሳችነት ነው» ስትል ጽፋለች። አንድ አገልግሎቱን የጨረሰ የወንጌል መልዕክተኛ የአገልግሎት ዘመናቸውን የጨረሱ አገልጋዮች ወደሚኖሩበት የጡረታ ቦታ መሄድ በጣም ይፈራ ነበር። ወደዚህ የጡረታ ቤት ከገባ ከጥቂት ወራት በኋላ በጻፈው ደብዳቤ ውስጥ «በእውነተኛ ደስታ እኳያ እነዚህን ሰዎች የሚመስሉ አጋጥመውኝ አያውቁም» በማለት አድናቆቱን ገልጿል።

ቻርለስ ስፐርጂን የተባለው ሰባኪ በስብከትህ ውስጥ ቀልድ ትጨምርበታለህ የሚል ትችት ቀርቦበት ሲመልስ «ምን ያህል ከቀልድ እንደምቆጠብ ብታውቁ ኖሮ ታመሰግኑኝ ነበር» የሚል መልስ ሰጥቷቸዋል። ሰዎችን ሊያስደስት በሚችል መንገድ መስበክን በመደገፍ ሲናገር «በስብከቶቼ ውስጥ እናንተን ፈገግ ሊያደርጓችሁ የሚችሉ ነገሮች ታገኙ ይሆናል፤ ታዲያ ምን አለበት? ሰባኪ መደሰት እንደሌለበት ወይም ፈገግ ማለት ኃጢአት መሆኑን አልተረዳሁም። ሰሚዎች ለአኩል ሰዓት ከሚያንቀላፉ ይልቅ ለደቂቃ ያህል ቢስቁ ሳይሻላቸው አይቀርም» ብሏል።

የሚስቅ ሰው ሃይማኖት እንደሌለው ሰው ተደርጎ ሊቆጠር ይገባዋል? ከቤተ ክርስቲያን ብዙ መልካም ነገሮች እንዲጠፉ ስንፈቅድ ኖረናል፤ ብዙ ዕንቁዎችንም በእሪያዎች ፊት ጥለናል። ቤተ ክርስቲያን ደስተኝነትንና ፈገግ ማለትን ከመቅደስዋ አስወጥታ ለድግስ ቤትና ለሌሎች የጭፈራ ቦታዎች አሳልፋ ስትሰጥ በመጥፎ ጎዳና ትጓዛለች።

ደስተኝነት በወንጌል አገልግሎት ጉዞ ውስጥ ከፍተኛ ሥፍራ አለው። አንድ የወንጌል አገልጋይ የደስተኝነት ስሜት የለውም ማለት ከፍተኛ ጉድለት አለበት ማለት ነው። አንድ ስዊዲናዊ የወንጌል መልዕክተኛ ወደ ሕንድ አገር ተመልሶ ለመሄድ ሲፈልግ ጓደኞቹ አገሩ ሞቃት ስለሆነ እንዳይሄድ መከሩት፤ በተጨማሪ እርሱ ሄዶ በሚሠራበት አካባቢ ጥላማ ነው በሚባለው ሥፍራ እንኳ የሙቀቱ መጠን በጣም ከፍተኛ መሆኑን ነገሩት፤ እርሱ ግን ሁልጊዜ በጥላ ውስጥ መሆን አለብኝ እንዴ በማለት መልሶላቸዋል።

እንደዚሁም በሕንድ ውስጥ ይሠራ የነበረ አንድ ሌላ አገልጋይ እንዲህ ሲል ተናግሯል፡- «የደስተኝነት ስሜት የጎደለው ታማኝ አገልጋይ አይቼ አላውቅም። ደስተኝነት ማለት ድንገተኛ ችግሮች ከሚፈጥሩት ጭንቀት ነፃ በመሆን ራሱንና ሁኔታዎችን በትክክለኛ አኳኋን መመልከትና አለመሸበር ማለት ነው።»

«ደስተኛ ያልሆነ አገልጋይ ሌሎችን ሊመራቸው አይችልም። በጌታ ሐሴት ማድረግና የደስተኝነት ስሜት የማይነጣጠሉ ናቸው።»

ሐምሳ ዓመታት ያህል እግዚአብሔርን ሲያገለግል የኖረ አንድ አገልጋይ፡- «በሕይወቴ ዘመን አገልግሎቱ ሲሳካለት ያየሁት የእግዚአብሄር ጸጋና እውነተኛ የደስተኝነት ስሜት ያለው ሰው ብቻ ነው» በማለት ተናግሯል። ደስተኝነት ለሰብከቶች ጥሩ መዓዛ፥ መልካም መስናዶና የአነጋገር ችሎታን ይሰጣል።

ደስተኝነት የስብከቱ ማጣጣሚያና ሰዎችን ለመቀስቀሻ ሲጠቀምበት የሚነገርለት አንድ ሰባኪ ነበር። አንዳንዴ ሲሰብክ ሰሚዎቹን ሳቅ ይፈነቅላቸውና ጉባዔው ይናጋ ነበር። ቢሆንም የተቀደሱ ነገሮች መሳቂያ እንዲሆኑ በፍጹም አይፈቅድም ነበር። ሰዎችን የሚያስቅ ነገር ከተናገረ በኋላ ወዲያውኑ ወደ ቁምነገሩ ይመለሳል፥ በዚህ ጊዜም ሰሚዎቹ የተሰማቸው ደስታ ሳይቀንስ ወደ ቁም ነገሩ ይመለሳሉ።

የሚያስቅ ነገር ተገቢ መሆኑን ወይም አለመሆኑን ማወቅ የምንችለው ልንቆጣጠረው እንችላለን ወይስ አንችልም የሚለውን ጥያቄ ስንመልስ ነው። ትክክለኛና ተገቢ የደስተኝነት ስሜት ያለው ሰው ቀልድ መቀለድ የሚችለው በየትኛው ቦታና ሰዓት መሆኑን ያውቃል፤ ስሜቱንም ይቆጣጠራል።

## ቁጣ

ይህ መመዘኛ ከሌሎቹ ሁሉ ለየት ያለ ሆኖ ይታያል። በሌላ በኩል ደግሞ ሰዎችን ለአገልጋይነት የማያበቃ ጸባይ መስሎ ሊታይ ይችላል። ኢየሱስ ክርስቶስ እንዲህ ዓይነቱ ጸባይ አልነበረውም ማለት ይቻላል? ኢየሱስ እንደተቆጣ ከዮሐ.2፡ 15-17 መመልከት እንችላለን። ተገቢ ቁጣ ከፍቅር ያነሰ ዋጋ ሊሰጠው አይችልም፤ ሁለቱም የእግዚአብሔር ባሕርያት ናቸው፤ ሁለቱም የማይነጣጠሉ ነገሮች ናቸው። ኢየሱስ የፈጸመውን የፈውስ ተዓምር በተቃወሙት ሰዎች ላይ እንዲቆጣ ያደረገው ለሰውየው የነበረው ፍቅር ነው፤ ማር.3፡5። ለአሕዛብ ሁሉ

የጸሎት ቤት የነበረውን የአባቱን ቤት የሌቦች ዋሻ ባደረጉት ነጋዴዎች ላይ እንዲቆጣ ያደረገው ለአባቱ የነበረው ፍቅርና ለአባቱ ክብር የነበረው ቅናት ነው፤ ማቴ.21፡13።

ዊልበርፎርስ የተባለው እንግሊዛዊ ባሮችን ነፃ ለማውጣት በምንም ነገር ሳይበገር በባርያ ነጋዴዎች ላይ ያሳየው ቁጣ ተገቢ ነበር። እንዲሁም እግዚአብሔርን በማያከብረውና ሰውን በባርነት በሚያስረው በፍትሕ መጓደል ላይ ያላንዳች ፍራቻ ተቆጥተው የተናገሩት ሰዎች ለሕዝብ ሁሉ ወደር የማይገኝለትን ሥራ ሠርተዋል።

ታዋቂው ሰባኪ ኤፍ ዳብልዩ ሮበርትሰን እንዲ በዚህ ዓይነት ቁጣ መናደዱን ሲያስታውስ፦ «ደሜ ልክ እንደ እሳት ቱግ አለ፤ በእጥንቶቼ ውስጥ ተሰምቶኝ የማያውቅ ብርታት ተሰማኝ፤ ለፈሪውና ለውሸተኛው የሚገባውን ቅጣት መስጠቴን አወቅሁ፤ በማወቁም ደስ አለኝ» ሲል ተናግሯል። እንዲ ማርቲን ሉተር ስለራሱ ሲናገር «ስሜቴ በጥቂቱ እስኪነሣሣ ድረስ በብርታት መሥራት አልችልም፤ ከዚያ በኋላ ግን ሳልቆጠብ ሥራውን ማጠናቀቅ እችላለሁ» ብሏል።

ቢሆንም እንዲህ ዓይነቱ ቁጣ ለወቀሳ የተጋለጠ ሊሆን ይችላል። ቁጣቸውን ወደ ኃጢአትነት ሳይለወጥ ሊያስተናግዱት የሚችሉት ጥቂት ሰዎች ብቻ ናቸው። ሰዎች ተገቢ ቁጣ ሊቆጡ የሚችሉ መሆናቸውን ጳውሎስ ሲገልጽ «ተቆጡ፤ ነገር ግን ኃጢአት አታድርጉ» ብሏል። ተገቢ ቁጣ በውስጡ ራስ ወዳድነት የለበትም። ራስ ወዳድነት ያለበት ቁጣ በኃጢአት የተሞላ ነው። ቁጣ ኃጢአት የሌለበት እንዲሆን ዓላማው እግዚአብሔርን ማክበር ሆኖ ለእውነትና ለንጽሕና በመቅናት የተደረገ መሆን ይገባዋል።

አንድ ምሁር ስለዚህ ቁጣ ሲያትት የሚከተሉትን አምስት መመዘኛዎች አቅርቧል።

1. ለራሳችን በማድላት ይኸውም ምንም ሳንጎዳ ጉዳት እንደደረሰብን ብንቆጣ፥

2. ለራሳችን አድልተን የተፈጸመብንን በደል ያለመጠን ብናጋንነው።

3. ሰዎች ባደረሱብን ችግር ወይም መከራ ምንም ሳንጎዳ ብንመረር፥

4. ንዴታችን ከመጠን አልፎ ወደቂጣ ቢለወጥና

5. መንሥኤ ቢኖረውም እንኳ በቀል ለመመለስ ሰውን ስንበድል ወይም ስንጎዳ ቁጣችን ኃጢአት ነው።

በሕይወታችን ውስጥ በሚገኘው ኃጢአት ላይ ትክክለኛ ፍርድ መስጠት ከቻልን ሌሎች ስለሚሠሩት ኃጢአት በሚገባ ልንቆጣ ሳንችል አንቀርም። ይህን ለማድረግ ከተለማመድን የምንገልፀው ቁጣ ትክክል ሊሆን ይችላል።

# ትዕግሥት

ትዕግሥት ለአገልጋይነት ከሚያስፈልጉት ነገሮች አንዱ ነው። ዮሐንስ አፈወርቅ የተባለው አበው «ትዕግሥት የመልካምነት ንግሥት ናት» ብሏል። ብዙ ሰዎች ለቃሉ የሚሰጡት ትርጉም ደካማ ባሕርይ ስለሚያስመስለው እውነተኛውንና የመጀመሪያውን የትዕግሥትን ሃሳብ

የሚያመለክት አይደለም። አንድ ምሁር በ2ጢሞ.1፡6 ላይ ሲያትት «ቃሉ የሚያሳየው እጆቹን አጣጥፎ ነገሮችን እንደ ቀላል የሚቆጥር መንፈስ አይደለም። ትዕግሥት ማንነትን ሳይለዋውጥ በፈተናዎች ውስጥ በድል አድራጊነት ጸንቶ መገኘት ነው። ትዕግሥት ክርስቲያናዊ ጽናት ነው፤ ኑሮ የሚያመጣብንን ማናቸውንም ነገር በድፍረት መቀበል ነው፤ እጅግ አስከፊ የሆነውን ነገር ወደ ከፍተኛው ደረጃ የመወጣጫ መሰላል አድርጎ መለወጥ ነው። ትዕግሥት ከባድ ነገሮችን መሸከምና ጉዟችንን እንድናቋርጥ የሚያደርጉንን ነገሮች አልፈናቸው እንድንሄድ፥ ዘወትርም ደግሞ የማይታየንን ነገር ከፍተኛ አቀባበል እንድናደርግለት የሚያበቃን ድፍረት የተሞላው ችሎታ ነው» ብሎ ተናግሯል።

የትዕግሥት ባሕርያት ጎልተው የሚታዩት ሰው ከሰው ጋር በሚያደርጋቸው ግንኙነቶች ውስጥ ነው። ጳውሎስ በማርቆስ ምክንያት ትዕግሥት ያጣበት ጊዜ ነበር። አንድ መንፈሳዊ መምህር «እምነት የጣልኩባቸው ሰዎች አደራ የሚበሉና በግድየለሽነት የሚሠሩ መሆናቸውን ስረዳ ትዕግሥት እጣለሁ። ትዕግሥት ማጣት ምንም ዋጋ የለውም፤ ዋጋ ያለው ቸርነት ብቻ ነው። ቢሆንም ይህ ለእኔ ፈተና ነው» በማለት ተናግሯል። ሌሎችም ብዙ መሪዎች ይህ ዓይነቱ ፈተና ይገጥማቸዋል፤ ታዲያ የተጠራጣሪው የቶማስ፥ የወላዋዩ የጴጥሮስና የከሐዲው የይሁዳ ባሕርያት የጌታችንን መልካም ትዕግሥት የቱን ያህል ፈትነውት ይሆን?

አንድ አገልጋይ ወደፊት በመሮጥ ተከታዮቹን ወደኋላ በመቅረታቸው ተስፋ ሊያስቆርጣቸው በሚችል ሁኔታ ላይ እንዳይጥላቸው ትዕግሥት ያሻዋል። አንድ አገልጋይ ከእነርሱ ፊት ቀድሞ መገኘት ቢኖርበትም እነርሱን በሚገባ መመልከትና ሲጠሩት ድምፃቸውን መስማት እንዲችል ከአጠገባቸው ርቆ መሄድ የለበትም። ለደከሙ ተከታዮቹ የሚያበረታታ ጉብዝና ማሳየት የማይችል ብርታት የጎደለው ሰው መሆን የለበትም። «እኛም ኃይለኞች የሆንን የደካሞችን ድካም እንድንሸከም ... ይገባናል፤» ሮሜ 15፡1። የሰዎች ድካም ትዕግሥት የሚያሳጣው አገልጋይ የሚሰጠው አመራር ጉድለት ያለበት ነው። ብርቱዎች የመሆናችን ማረጋገጫው ሌሎችን ወደኋላ በመተው ወደ ፊት ርቀን መራመዳችን ሳይሆን ከደካሞች ወንድሞቻችን እርምጃ ጋር እኩል እየተራመድን አገልግሎት ከመስጠት አለመቆጠባችን ነው። ሌሎችን ወደኋላ ትተን እጅግ ወደፊት ርቀን ብንሄድ እነርሱን የራሳችን ተከታዮች ለማድረግ ያለንን ችሎታና ኃይል እናጣለን።

አንድ መንፈሳዊ ሰው:- «ሌሎችን መልሶ ባለመተቸትና ባለመቃወም የሚሰነዘርበትን ትችትና ተቃውሞ ሁሉ ይቀበል ነበር። ክርስቲያን ስለ ክርስቶስ ሲል ትዕግሥተኛ፥ ተስፋ የማይቆርጥና መከራን የሚቀበል መሆን አለበት። የስድብ ማዕበል ሲገጥመውም ምንም ስሜት ሳይሰማው መጋፈጥ አለበት። በእርሱ ላይ ለማላገጥ የሚሰነዘሩበትን ስድቦች በጸጥታ መቀበል ይኖርበታል። ዓለምን መለወጥ የሚችሉ እነዚህን ሁኔታዎች ተጋፍጠው የሚቆሙ ሰዎች ብቻ ናቸው» ሲል ስለ አባቱ የነበረውን ሃሳብ ጽፏል።

አንድ አገልጋይ በኃላፊነት ከተሰጡት ሥራዎች መካከል አስፈላጊ ናቸው ብሎ የሚያምንባቸውን ዕቅዶች በሥራ ላይ ከማዋሉ በፊት ከፍተኛ ትዕግሥት ያስፈልገዋል።

አንድ ሰው ስለ ሃድሰን ቴይለር ሲናገር:- «ከዚህ አንጻር ከሃድሰን ቴይለር የተማርኩትን ነገር ፈጽሞ አልረሳውም። በተደጋጋሚ ለሥራ የሚበጁና የሚጠቅሙ ለውጦች በተግባር ላይ ለማዋል ሲፈልግ ከባልደረባዎቹ ብዙ ተቃውሞ ይገጥመው ስለነበረ ከጥቅሙ ይልቅ ጉዳቱ

ማመዘኑን ተረድቶ ሁሉን ነገር እርግፍ አድርጎ መተዉን አይቻለሁ። የኋላ ኋላ ግን በጸሎት ብዙ በመትጋቱ ያለምንም ተቃውሞ እነዚህን ለውጦች ማከናወን ችሏል» ብሏል።

## ተግባቢነት

በአመራሩ ውስጥ ከሰዎች ሁሉ ጋር መግባባት እንደሚችል ይነገርለት የነበረ አንድ መንፈሳዊ አገልጋይ ነበር። በአካባቢው የነበሩትንና እንዲያውም ሰዎችን ሁሉ ይወድ ነበር። ስለዚህ ሰው የተነገሩት አባባሎች መንፈሳዊ አገልጋይ ሰዎችን መውደድ ያለበትና ከሰዎች ጋር ለመግባባት ከፍተኛ ችሎታ የሚያስፈልገው መሆኑን ያሳያሉ። ዳዊት ሊሞቱለት ዝግጁ የነበሩትን ሰዎች በሥልጣኑ ሥር ሊያፈራ የቻለው የማሰባሰብ ችሎታው ከፍተኛ በመሆኑ ነበር። እነዚህ ሰዎች ፍጹም ለእርሱ ተማርከው ስለነበረ በሹክሹክታ የተነገረው የእርሱ ፍላጎት እንኳ እንደ ትዕዛዝ ተደርጎ ይቆጠር ነበር! 2ሳሙ.23፡15-16። እርሱ ስለ እነርሱ እንደሚሞት ያውቁ ስለነበር ሊሞቱለት ዝግጁ ነበሩ።

ጳውሎስም እንዲህ ዓይነቱ የመግባባት ችሎታ ነበረው። ማለትም ሰዎችን ወዳጆቹ የማድረግ ከፍተኛ ችሎታ ነበረው። በአዲስ ኪዳን ውስጥ እንደ ጳውሎስ አስፈሪ ጠላቶች የተነሡበት ማንም ሰው አልነበረም! እንደ ጳውሎስ መልካም ጓደኞች የነበሯቸው ሰዎች ቁጥርም እንዲሁ በጣም ጥቂት ነው። የእነርሱን ማንነት ለይቶ ማወቅ እስከማይችል ድረስ ከእርሱ ጋር የጠበቀ ግንኙነት ነበራቸው።

ጳውሎስ ታላቅና ዓላማው ግቡን የመታለት አገልጋይ ሊሆን የቻለው ይግባባቸው ከነበሩ ሰዎች ጋር ጥልቅ የሆነ ፍቅርና ታማኝነት የተሞላበት ግንኙነት በፈቃደኝነት ላይ ይመሠርት ስለነበር ነው። ለወንጌል ሥራና ለክርስቶስ ሲል በሚያከናውናቸው በማናቸውም ተግባራት ከጓደኞቹ ጋር ይተባበር ነበር። እነርሱም እርሱ የሚወዳቸው ለመሆኑ እርግጠኞች ስለነበሩ ደስ እያላቸው ይከተሉት ነበር። አብረውት ይሠሩ ለነበሩ ሰዎችም ምን ያህል ጥልቅ ፍቅር እንደነበረው የጻፋቸው መልዕክቶች ያሳያሉ።

በአገልግሎት ውስጥ አስፈላጊ የሆነው ሌላው ነገር ሰዎች የተሻለውን ነገር እንዲያከናውኑ ማድረግ መቻል ነው። ይህንንም ለማከናወን ከሰዎች ጋር ረዥም ክርክር አድርጎ ከመርታት ይልቅ በግል ጓደኝነት ኃይል ማሳመን ይበጃል። ሰዎች ሃሳብ ለሃሳብ በመለዋወጥ መንገድ መረዳት ቢሳናቸውም በልባዊና እውነተኛ ጓደኝነት ሊሸነፉ ይችላሉ።

ታማኝ መንፈሳዊ አገልጋዮች ሁሉ ታላቅ ፍቅር ያላቸው ሰዎች ናቸው።

ሰዎችን በጥልቅ ፍቅር መውደድን የሚተካ ምንም ነገር የለም። ይህ ተሰጥዎ ያላቸው ሰዎች ከፍተኛ ኃይል አላቸው። ከፍተኛ የማስተዋል ችሎታ ለብቻው ምንም ሊሠራ አይችልም። የመጽሐፍ ቅዱስ ዕውቀትም በቂ አይደለም። አንድ መንፈሳዊ አገልጋይ ሰዎችን ለራሳቸው ጥቅም ሲል መውደድ አለበት። በአጠገቡ የሚገኙት ሰዎች ከማናቸውም ዓይነት ጎሣ ይሁኑ፥ ማንኛውም ዓይነት ቀለም ወይም መልክ ይኑራቸው፥ ነገር ግን ስለ እነርሱ ደስታ ሊሰማው ይገባል።

ታላቁ አገልጋይ ቻርልስ እስተርጅን በኖሩበት ዘመን ከነበሩት አገልጋዮች መካከል የርሳቸውን ያህል መንፈሳዊ ሥልጣናቸውን የተጠቀሙበት ሰዎች በጣም ጥቂት ናቸው። አንድ ሰው ስለ እርሳቸው ሲጽፍ፡- «ሰዎች ያለምንም ጥርጣሬ ይከተሏቸው ነበር! ይህም ሊሆን

የቻለው በእርሳቸው ጠባይ ማራኪነት ሰዎች ስለተሸነፉ ሳይሆን እነርሱ እሳቸውን ይወዷቸው ስለነበር ነው። የእኚህ ሰው ሥልጣን በጥበብና በፈቃደኝነት ላይ የተመረኮዘ ስለነበር በሰዎች ዘንድ ተቀባይነት አትርፏል» ብሏል።

ከጳውሎስና ከዳዊት የበለጠው መሪ ይኸውም ጌታ ኢየሱስ ተከታዮቹን በወዳጅነትና በጥልቅ ፍቅር መምራት ችሏል። በዮሐ.13፡1 «በዚህ ዓለም ያሉትን ወገኖቹን የወደዳቸውን እስከመጨረሻ ወደዳቸው» ተብሎ ስለ ኢየሱስ ተጽፏል። ጴጥሮስ በዮሐ.21፡17 «ጌታ ሆይ አንተ ሁሉን ታውቃለህ፤ እንድወድህ አንተ ታውቃለህ» የሚለውን ከተረታ ልብ የወጣ ኑዛዜ እንዲናዘዝ ያደረገው ኢየሱስ በጥልቅ ፍቅር የሚወደው መሆኑን ማወቁ ነው።

## ብልሐትና የአዕምሮ ንቃት

እነዚህ ሁለቱ የቅርብ ግንኙነት ያላቸው ናቸው። ብልሐት ማለት ነገሮችን የመረዳት ኃይልና ችሎታ ነው፤ በተለይም ፍጥነትና ጥረት ባለው መንገድ ተስማሚ፣ ተገቢ ወይም ትክክል የሆነውን ሊረዳ ወይም ሊነገር የሚገባውን ነገር ማሰብ ነው። ከሌሎች ጋር ግጭት የሚፈጥሩ ነገሮችን የማስወገጃ ዘዴ ነው። የአዕምሮ ንቃት ደግሞ ማናቸውንም ጉዳይ ለማከናወን የሚያስችል ችሎታ ነው። ብልጥና በአዕምሮአቸው ንቁ የሆኑ ሰዎች ብዙ ጊዜ ስድብን የሚጠቀሙ በመሆናቸው ብልጥ የሚለው ቃል ሊጥላላና ሊናቅ ችሏል። የሁለቱ ታላቅ መጣመር ግጭትንና አድር ባይነትን ባለመጠቀም ተቃራኒ ነገሮችን የማስማማት ችሎታን ያመለክታል። እነዚህ ችሎታዎች ለቤተ ክርስቲያን አመራር በዋጋ ሊተመን የማይችል ጥቅም አላቸው። የሁለቱንም ወገኖች መብቶች በመጠበቅ ውስብስብ የሆኑ ተግሳጽ ቀመስ ውይይቶችንና በሰዎች መሃከል የተፈጠሩ አለመግባባቶችን ወደ ተስማሚ ውጤት እንዲደርሱ የማድረግ ችሎታ ሰው ሁሉ ሊመኘው የሚገባ ታላቅ ሀብት ነው። ይህም ችሎታ ራስን በተግሳጽ ቀመስ ውይይቶቹና በአለመግባባቶቹ ውስጥ ባሉት ሰዎች በታ ማስቀመጥንና ምን ዓይነት ስሜት እንደሚሰማቸው እንዲሁም ምን እንደሚያደርጉ መገመትን ይጠይቃል።

ምንም ነገር ብልሐት በተሞላው ወይም ብልሐት በጎደለው መንገድ መናገር ይቻላል። አንድ ጫማ ነጋዴ ለአንድ ደምበኛው እንዲህ አላት፡- «አዝናለሁ እመቤቴ እግርዎ ትልቅ በመሆኑ ይህ ጫማ አይበቃዎትም።» ሌላው ጫማ ነጋዴ ደግሞ በተመሳሳይ ሁኔታ ውስጥ ለነበረች አንዲት ሴትዮ፡- «አዝናለሁ እመቤቴ ይህ ጫማ በጣም ትንሽ በመሆኑ ለእርስዎ አይበቃዎትም» አላት። ሁለቱም የተናገሩት ተመሳሳይ ቃላት ነው፤ ነገር ግን ብልሐትና የአዕምሮ ንቃት ሁለተኛው ነጋዴ መለስተኛ የሆነ ልዩነት ባለው አነጋገር ተናግሮ በአገልግሎቱ የምትረካ ታማኝ ደምበኛ ማፍራት ችሏል።

ኢያሱ የተስፋይቱን ምድር ለእስራኤላውያን ለማከፋፈል በብልሐትና በአዕምሮ ንቃት የተጠቀመበት መንገድ ርዕሱን ለማብራራት ጥሩ ምሳሌ ነው። እባቱን ያታልል ከነበረው ከያዕቆብ በተወለዱት ሕዝብ መሃከል የተፈጠሩትንና ሊበታትኗቸው ይችሉ የነበሩትን የከረሩ አለመግባባቶች ኢያሱ ማስወገድ ችሏል። በሕዝቡ መሃከል የነበሩት ችግሮች፣ ጥሎች፣ ስግብግብነትና ራስን መውደድ የተሞሉ ከመሆናቸውም በላይ ኢያሱ የፈጸመው ተግባር እጅግ ውስብስብ ነበር። ኢያሱ ይህንን ተግባር ለመፈጸም የተጠቀመበት ብልሐት የተሞላው መንገድ እርሱ ጠቢብ መሆኑን ብቻ ሳይሆን ከእግዚአብሔር ጋር የቅርብ ግንኙነት የነበረው ሰው መሆኑን ያሳያል። የሮቤልና የጋድ ነገዶች ሌላ መሠዊያ በመሥራታቸው የተፈጠረውን መራራ ግጭትና

አለመግባባት ለማስወገድ የተጠቀመበት ዘዴ ኢያሱ እግዚአብሔር ጥበብን ያስተማረው ሰው የመሆኑ ማስረጃ ነው።

ዊልያም ኬሪ የተባለው የቤተ ክርስቲያን አገልጋይ በተፈጥሮው በጣም ዘዴኛ ነበር፤ ከጓደኞቹ አንዱ ስለ እርሱ ሲጽፍ፡- «ሌሎች ሰዎች የእርሱ የበታች መሆናቸውን ሳይረዱት የማስተዳደር ችሎታ ነበረው፤ ይህንንም ያደርግ የነበረው ዕቅድ እያወጣ መሆኑን በፍጹም አይታይም ነበር» በማለት ስለ እርሱ መስክሯል። ሰው አስቦና አቅዶ ሲጠቀምባቸው ብልሐትና የአዕምሮ ንቃት በጣም ፍሬያማ ናቸው።

## የማነቃቃት ችሎታ

ለአገልጋይነት በእግዚአብሔር የመመረጥ አንዱ ምልክት ሌሎች እንዲያገለግሉ የማነቃቃት ችሎታ ነው። በአገልግሎቱ የሚቃጠል አገልጋይ በአካባቢው ያሉትንም ሰዎች ያነሣሣቸዋል። እያሌ የተባረኩ የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች ብዙ ሥራዎች ከመሥራታቸውም በላይ ጓደኞቻቸውም ደግሞ በርትተው እንዲሠሩ ሊያነቃቋቸው ችለዋል። የእነርሱ ቅንአትና ትጋት የሚዛመት ነው።

ፓስተር ሼይ በዘመኑ ከነበሩት ከቻይና ቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች መካከል ታዋቂ ነበር። ሌሎችን የማነቃቃት ችሎታም ነበረው። ከእርሱ ጋር ሆኖ ጌታን ያገለግል የነበረ አንድ ሰው «የቤተ ክርስቲያንህ መጋቢ ሌሎችን ለመምራትና እርሱን እንዲቀበሉት ለማድረግ ስለሚፈጽመው ተግባር የምታስታውሰው ነገር አለህ?» የሚል ጥያቄ ቀርቦለት ሲመልስ፡- «በዚህ ረገድ ከፍተኛ ኃይል እንዳለው እረዳለሁ፤ ምንም ዓይነት ጥረት ሳያደርግ ሰዎችን ማንቀሳቀስ ይችላል፤ ሰዎች ይከተሉታል፤ እንዲሁም ያምኑበታል፤ ስለዚህም ሰዎችን የመቀስቀስ ልዩ ከፍተኛ ኃይል አለው። እርሱ ባለበት አካባቢ የሚገኝ ሰው ስለ ክርስትና ሕይወትና አገልግሎት አዲስ ትምህርት ያገኛል» በማለት ተናግሯል።

ነህምያም ከዚህ ጋር ተመሳሳይ የሆነ የተትረፈረፈ ኃይል ነበረው። እርሱ ወደ ኢየሩሳሌም በደረሰበት ወቅት ሕዝቡ ልባቸው ዝሎ መንፈሳቸው ተዳክሞ ነበር። ብዙ ጊዜ ሳይፈጅበት ብርቱ ሠራተኞች አድርጓቸዋል። በነህ.4፡6 «የሕዝቡም ልብ ለሥራው ጨክኖ» የሚለውን ከማንበባችን በፊት ነህምያ ሌሎችን የመምራት ኃይል እንደነበረው እንመለከታለን። ነህምያም ያን ዓይነቱን መመሪያ ባይሰጥ ኖሮ ቅጥሩን የመገንባቱ ሥራ በፍጹም አይጀመርም ነበር ማለት ነው።

## የማስተዳደር ችሎታ

ይህ ችሎታ የሚጎድለው ሰው ምንም ያህል ነገሮችን መንፈሳዊ አድርጎ ቢመለከታቸውም እንኳ በፊቱ ያለውን ራዕይ በተግባር ሊገልጽ አይችልም። የአንድ ተቋም አስተዳደር ውስብስብ ሲሆን ብዙ ችግሮች ሊፈጠሩ ይችላሉ፤ ይህም የመንፈስ ቅዱስን መሪነትና አሠራር ሊያርቅ ይችላል። ሆኖም የአስተዳደር ቅልጥፍና ዘወትር መንፈስ ቅዱስን ያርቃል ማለት ተገቢ አይደለም። የድርጅትና የአሠራር ጉድለት ራሱን የቻለ አደጋ ነው፤ ለእግዚአብሔር ብዙ ተግባር ሊፈጽሙ ለሚችሉ ለብዙዎቹ ተቋሞች የውድቀት ምክንያት ሆኗል።

አንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ምሁር በትንቢተ ኢሳይያስ ውስጥ የሚገኘው «ፍርድ» ተብሎ የተተረጎመው ቃል «የአሠራር መንገድን፥ ሥርዓትን፥ ዘዴንና ሕግን» ያመለክታል የሚል ሃሳብ አቅርቧል። ስለዚህ ኢሳይያስ «እግዚአብሔር የፍርድ አምላክ ነው» በሚልበት ጊዜ እግዚአብሔር የአሠራር መንገድ ያለው አምላክ መሆኑን ያመለክታል፤ ኢሳ.30፡18። የፈጠራቸው ፍጥረታት በሥርዓት የተሞሉ ናቸው። እግዚአብሔር የሥርዓት አምላክ በመሆኑ አገልጋዮች እንዲሆኑ የሚፈቅድላቸውም ሰዎች ማናቸውንም ነገር በሥርዓት እንዲያከናውኑ ይፈልጋል ማለት ነው። ሁሉን ቻይና ምሕረትን የተሞላው አምላክ ለሁሉም ነገር የአሠራር መንገድ ያለው ነው። እነዚህን ሦስት ባሕርያት በሚገባ ያላቀፈ ትምህርት የተሟላ ወይም የተስተካከለ ነው ማለት አይቻልም።

ለእግዚአብሔር በምንሠራቸው ሥራዎች ውስጥ በተቻለን መጠን የእግዚአብሔርን ሥርዓትና የአሠራር መንገድ መከተል የእኛ ፋንታ ነው። በአስተዳደር ብልሐት ሰዎችን ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ልናስገባቸው ባንችልም በመንፈስ ቅዱስ ምሪት በመደገፍ እግዚአብሔር ለእነርሱ ባዘጋጀው የደኅንነት ዕቅድ ውስጥ በሚገኘው የአስተዳደር ዘዴዎች መጠቀም አያስፈልገንም ማለት አይደለም።

አንድ ምሁር ስለ ጆን ወስሊ ሲጽፍ፡- «የአስተዳደር ችሎታው ከየትኛውም ርዕሰብሔር የማያንስ ነበረ» ብሏል።

አንድ መንግሥት ለሕዝብ ከሚሰጠው አመራር በማያንስ መንገድ ለተከታዮቻቸው መመሪያ የሰጡ የሃይማኖት መሪዎች ነበሩ። የአሠራራቸውም ጥንካሬ በመሠረቱት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ እስካሁን ይታያል። የመሠረቷት ቤተ ክርስቲያን እነርሱ ከሞቱ በኋላ ሳትናወጥ ጸንታ መቆሟ የሚያሳየውም ይህንኑ ነው።

አንድ አገልጋይ የሰዎችን ጸባይና ባሕርይ የመገምገም ችሎታ፥ ከሰዎች ጋር የመሥራት ዓቅሙ፥ ሰዎች ከፍተኛ ጥቅም የሚሰጥ ሥራ እንዲሠሩ ማድረጉና ሰዎች በታማኝነት እንዲገዙለት የማድረግ ሥልጣን ሲኖረው ቤተ ክርስቲያንን ከብዙ ችግር ያድናታል።

# ምዕራፍ 9

## ለአገልግሎት እጅግ አስፈላጊ የሆነው ነገር

«መንፈስ ... የሞላባቸውን ሰዎች ምረጡ፤ መንፈስ ቅዱስም ... የሞላበትን ሰው እስጢፋኖስን ... መረጡ፤» የሐዋ.6፡3፥ 5።

መንፈሳዊ አገልግሎት ለመስጠት የሚችሉ በመንፈስ የተሞሉ ሰዎች ብቻ ናቸው። ሌሎችም ነገሮች ለመንፈሳዊ አገልግሎት አስፈላጊ ናቸው፤ በመንፈስ መሞላት ግን በጭራሽ ሊጓደል የማይገባው ነው።

ስለ መንፈሳዊ አገልግሎት የተሰጡት መመሪያዎች ምንጭና በመንፈስ ቅዱስ መሪነት የተጻፈው የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ቤተ ክርስቲያንን የመሠረቱት ሰዎችና የወንጌል መልእክተኝነት ተግባር ታሪክ ነው። በመጀመሪያይቱ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ በሰው ግምት

አንስተኛ ናቸው የሚባሉትን አገልግሎቶች እንኳ ለማከናወን ይመረጡ የነበሩት ሰዎች ዋና መመዘኛ በመንፈስ ቅዱስ የተሞሉ መሆናቸው ነበር። በቀና ጸባያቸውና በብልህነታቸው የታወቁ መሆን ቢያስፈልጋቸውም ከዚያም ባሻገር በክርስትና ሕይወታቸው የበሰሉ መሆን ነበረባቸው። ሰው በአስተሳሰቡ ምንም ያህል ብልህ ቢሆንም የቱንም ያህል የማስተዳደር ችሎታ ቢኖረውም በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ ካልሆነ በቀር እውነተኛ መንፈሳዊ አመራር መስጠት አይችልም።

የሐዋርያት ተግባራት መንሥኤ የመንፈስ ቅዱስ አመራር መሆኑ በገልፅ ይታያል። የቤተ ክርስቲያን የበላይ አስተዳዳሪና የወንጌል መልዕክተኝነት ተግባር ዋና ዕቅድ አውጪ በመሆን ልዩ ሥራዎችን ሠርቷል። መንፈስ ቅዱስ ለሥልጣኑ የሚቀናና ሥጋውያን የሥልጣኑና የኃይሉ ወኪሎች እንዲሆኑ የማይፈቅድ መሆኑን መረዳት ይቻለናል። ተግባራቸው የቤተ ክርስቲያን ጊዜያዊ ጉዳዮችን ማከናወን የሆነ ሰዎች እንኳ በመንፈስ ቅዱስ ቁጥጥር ሥር ሊሆኑ ይገባል። እነዚህ ሰዎች መመረጥ ያለባቸው በምድራዊ ጥበብ ደረጃ፥ የሀብት አያያዝ ችሎታ ወይም በሰዎች ዘንድ ባላቸው ተቀባይነት ሳይሆን ቀዳሚ ዋጋ ሊሰጠው በሚገባው በእውነተኛ መንፈሳዊነታቸው ነው። ቤተ ክርስቲያን ወይም ሌላ ክርስቲያናዊ ተቋም ከዚህ አሠራር ዝንፍ ሲል መንፈስ ቅዱስን ከመሪነት ሥፍራው ያስወግደዋል ማለት ነው። በዚህም ምክንያት መንፈስ ቅዱስ ያዝናል፤ ሊሠራም አይችልም፤ ውጤቱም መንፈሳዊ ረሃብና ሞት ይሆናል።

መንፈሳዊ መመዘኛዎችን ባለመከተላችን ለቤተ ክርስቲያን ወይም ለሌሎች መንፈሳዊ ሥራዎች የሚሆኑትን አገልጋዮች ብንመርጥ ያለማወላወል መንፈሳዊ ያልሆነ አስተዳደር መመሥረታችን ነው። አንድ ምሁር ከዚህ አሠራር የተነሣ የሚፈጠረውን ሁኔታ ሲገልፅ «ቁጥጥርን የሚጠላ ሰፊ ማኅበር ይመስላል» ብሏል። በዚህ ዓይነቱ ድርጅት ውስጥ ቀስ በቀስ ያለውን አስተዳደርና መንፈሱን የሚቃወሙ ሰዎች መነሣት ይጀምራሉ። እነዚህ ሰዎች መሪያቸው የሚወስደውን እርምጃ መቃወምና ዕቅዶቹን ማደናቀፍ ይቀጥላሉ። መሪው ከትብብር እና ከድጋፍ ይልቅ ቸልተኛና ምንም ለመሥራት የማይፈልጉ ሰዎች ያጋጥሙታል፤ እስከ መጨረሻው ደቂቃ ድረስ የከረረ ተቃውሞ ባይደርስበትም ሥራውን ለማከናወን ስለማይችል ኃላፊነቱን ለመልቀቅ ይገደዳል። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሥጋዊ የሆኑ ሰዎችን መሾም መንፈስ ቅዱስ ለቤተ ክርስቲያን ያለውን ዕቅድ እንዳያከናውን ያደርገዋል።

ሰዎች ፈቃደኞች ካልሆኑ መንፈስ ቅዱስ ሊጠቀምባቸው አይፈልግም። ከእርሱ ጋር ተባብረው ለመሥራት ፍላጎት የሌላቸውና መንፈሳዊነት የጎደላቸው ሰዎች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ መመረጣቸውን ሲመለከት እነዚህ ሰዎች እንደ ራሳቸው ፍላጎት ዕቅዳቸውን እንዲፈጽሙ በታውን ይተውላቸዋል፤ በምንም ነገር አይረዳቸውም። የዚህም ውጤት መንፈሳዊነት የጎደለው አስተዳደር ይሆናል።

በኢየሩሳሌም የነበረችው ቤተ ክርስቲያን የሐዋርያትን ምክር የምትሰማና የምትቀበል ነበረች። በዚህም መሠረት የተጠየቁትን መመዘኛዎች የሚያሟሉ ሰባት ሰዎች መርጣለች። እነዚህ ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ተመርተው ከፈጸሙት ተግባር የተነሣ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ተፈጥሮ የነበረው ቅሬታ ተወገደ፤ ቤተ ክርስቲያኒቱ ተባረከች። ምድራዊ የሆኑ ጥቅሞችን ለመስጠት ተመርጠው የነበሩ ሰዎች የመንፈስ ቅዱስ ተወካይ በመሆናቸው ሰማያዊ በረከት ሊሰጡ ችለዋል። እስጢፋኖስ ለክርስቶስ የመጀመሪያው ሰማዕት ሆነ፤ የእርሱም ሞት ለጳውሎስ ሕይወት መለወጥ ከፍተኛ አስተዋጽዖ አበርክቷል። ፊልጶስ ሐዋርያት ካልሆኑት ሰዎች መሃከል የመጀመሪያው ወንጌላዊ ሆነ፤ መንፈስ ቅዱስ በሰማርያ የተነሣው የታላቅ

መነቃቃት መሪ አደረገው። አገልጋዩ በተፈጥሮና በጸጋ ስጦታዎቹ በታማኝነት ከተጠቀመባቸው ልዩ የአገልግሎት ዕድል ሳያገኝ አይቀርም፤ ተጨማሪ ስጦታዎችም ሊቀበል ይችላል።

በመንፈስ ቅዱስ የተሞሉ ሰዎች ለክርስትና እንቅስቃሴ ከፍተኛ አስተዋፅዖ ያበረከቱ መሆናቸው በሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ ውስጥ በግልጽ ይታያል። ደቀ መዛሙርቱ ከላይ ኃይል እስኪቀበሉ ድረስ በኢየሩሳሌም ከተማ እንዲቆዩ ያዘዛቸው ኢየሱስ ራሱ «በመንፈስ ቅዱስ በኃይልም ተቀባ» ተብሎ በሐዋ.10፡38 ተነግሮለታል። ይህ ዕድል የተሰጣቸው 120 ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ተሞሉ፤ የሐዋ.2፡4። ጴጥሮስ ለአይሁድ መሪዎች ጉባዔ ንግግር ባደረገበት ወቅት በመንፈስ ተሞልቶ ነበር፤ የሐዋ.4፡8። እስጢፋኖስ በመንፈስ ተሞልቶ ማንም ሊቋቋመው በማይችል ሁኔታ ስለ ክርስቶስ ምስክርነት በመስጠትና ዘወትር ሲታሰብ በሚኖር አኳኋን ሞቷል፤ የሐዋ.6፡3፥ 5፤ 7፡55። ጳውሎስ ልዩና አስደናቂ የሆነውን አገልግሎት የጀመረውና የሰጠው በመንፈስ ቅዱስ ሙላት ውስጥ ሆኖ ነው፤ የሐዋ.9፡17፤ 13፡9። ከእርሱ ጋር በመዘዋወር የወንጌል አገልግሎት ሲሰጥ የነበረው ባርናባስም በመንፈስ የተሞላ ሰው ነበር፤ የሐዋ.11፡24። ከእነዚህ ምሳሌዎች ከሁሉ የሚበልጥ የመንፈሳዊ አገልግሎት መመዘኛ ምን እንደሆነ መገንዘብ የማይችል ሰው በእውነትም ዓይኑ የታወረ ነው።

እነዚህ ሰዎች ሁሉን የሚቆጣጠር አመራር ይሰጥ የነበረውን የመንፈስ ቅዱስን ምሪት ይከተሉ ነበር። በፈቃደኝነት ራሳቸውን በእርሱ ቁጥጥር ሥር ስላስገዙ የእርሱን መመሪያ ለመታዘዝ እንዲሠሩ የሚያነሣሣቸውንም ነገር ለመሥራት ደስተኞች ነበሩ። ፊልጶስ በሰማርያ የነበረውን ደስ የሚያሰኝ የመነቃቃት ሥራ ትቶ እንዲሄድ መንፈስ ቅዱስ ሲያነሣሣው ወደ በረሃ ነው የምሄደው ብሎ አንዳችም ተቃውሞ ሳይፈጥር ትዕዛዙን ተቀብሎ ሄዷል። በበረሃ ውስጥም ሰዎችን ወደ እግዚአብሔር ለማምጣት ይሠራ ነበር፤ የሐዋ.8፡29። የጴጥሮስን መገደርደር ያስወገደውና ወደ ቆርኔሌዎስ ቤት ሄዶ ሊገመት የማይቻል በረከት ለአሕዛብ እንዲፈስ ያደረገው መንፈስ ቅዱስ ነው፤ የሐዋ.10፡19፤ 11፡12። መንፈስ ቅዱስ ሳውልንና በርናባስን ጠርቶ የመጀመሪያዎቹ የወንጌል መልዕክተኞች አድርጓቸዋል፤ የሐዋ.13፡1-4። ጳውሎስ ለወንጌል አገልግሎት ባደረጋቸው ጉዞዎች ውስጥ እንዲያደርግም ሆነ እንዳያደርግ የሚሰጠውን ትዕዛዝ ሁሉ በማክበር ለመንፈስ ቅዱስ ታዛዥ ሆኗል፤ የሐዋ.16፡6-7፤ 19፡21፤ 20፡22። የታወቁት የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በኢየሩሳሌም ባደረጉት ስብሰባ ለመንፈስ ቅዱስ አመራር ሥፍራ ሰጥተውት ነበር። የጉባዔውን ውሳኔ ያስታወቁት «እኛና መንፈስ ቅዱስ ፈቅደናል» በሚል አነጋገር ነበር።

መንፈስ ቅዱስ በሰዎች ሥራ ጣልቃ ይገባ የነበረበት ምክንያት ወንጌልን ለአሕዛብ ለማዳረስ እንደሆነ መዘንጋት የለብንም። አሁንም ሆነ ያን ጊዜ ዓላማው ቤተ ክርስቲያንን የወንጌል መልዕክተኛ ማድረግ ነው። ታዲያ የእርሱ ዓላማ የእኛ ዓላማ ሊሆን አይገባም?

የወንጌል አገልግሎትን ሥራ ከሚያበረታቱትና ለአገልግሎቱ አዲስ ራዕይ ከሚሰጡት ዋና ዋና ነገሮች መካከል አንዱ 在ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚታየው መንፈሳዊ እንቅስቃሴ ነው። የመንፈስ ቅዱስ እንቅስቃሴ የታየባቸው ቀድሞ የወንጌል አገልጋዮችን በመላክ ተሳትፎ ያልነበራቸው አብያተ ክርስቲያናት ከእንቅስቃሴያቸው በኋላ በርካታ ተጓዥና እጅግ ጠቃሚ የወንጌል መልዕክተኞችን ማፍራት ችለዋል።

ጳውሎስ በኤፌሶን ለነበሩት የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የሰጠው ምክር ተግባራቸውን በምን ዓይነት መንገድ ሊገልጹ እንደሚገባቸው ፍንጭ ይሰጣል። «የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን ትጠብቁ ዘንድ መንፈስ ቅዱስ እናንተን ጳጳሳት አድርጎ ለሾመበት ለመንጋው ሁሉና ለራሳችሁ ተጠንቀቁ፤» የሐዋ.20፡28። የቤተ ክርስቲያን መሪ መሆን የቻሉት ሐዋርያት ስለመረጡዋቸው ወይም በሕዝብ ዘንድ ተወዳጅነትን ስላተረፉ አልነበረም፤ የተመረጡት በመለኮታዊ ምርጫ ነበረ። ለቤተ ክርስቲያን ብቻ ሳይሆን ለመንፈስ ቅዱስም ተጠሪ ናቸው። ታዲያ ይህንን ማወቅ ለእነርሱ ምን ዓይነት ማረጋገጫና ኃላፊነት እንዲሁም ምን ዓይነት መንፈሳዊ ሥልጣን ይሰጣቸው ይሆን?

መንፈስ ቅዱስ በሐዋርያት ላይ የወረደበት ዓላማ ወዲያውኑ ተግባራዊ ሆኗል። ሐዋርያት ያለ እግዚአብሔር ኃይል ማለትም በሰው ኃይል ብቻ ሊሠሩት የማይችሉት ሥራ ገጥሟቸው ነበር። በመንፈስ ቅዱስ መሞላታቸውም ለቆሙለት፥ ለተጠሩለትና ፋታ ለማይሰጠው አገልግሎት አስፈላጊ የሆነውን ኃይል ሰጥቷቸዋል፤ ሉቃስ 24፡29፤ ኤፌ.6፡10-18።

ቀለል ባለ መንገድ ሲገለጽ በመንፈስ መሞላት ማለት በፈቃደኝነት ራስን ለእግዚአብሔር መስጠትና በመንፈስ ቅዱስ ቁጥጥር ሥር መሆን ማለት ነው። መሞላት የሚለውም ቃል ይህንኑ ሃሳብ ይደግፋል። ቃሉ የአንድን ፈሳሽ ባዶ ወደሆነ ዕቃ ውስጥ መግባት አያመለክትም። የአንድ ሰው አዕምሮ በአንድ ነገር ከተያዘ ያ አዕምሮ የያዘው ነገር ሞልቶታል ማለት ነው። ቃሉ በሉቃስ 5፡26 ውስጥ ተመሳሳይ ሁኔታ ለማመልከት «ፍርሃት ሞላባቸው» ተብሎ ተጠቅሷል፤ ኢየሱስም በዮሐ.16፡6 «ይህንን ስለተናገርኋችሁ ሃዘን በልባችሁ ሞልቷል» በማለት ተናግሯል። የእነርሱ ፍርሃትና ሃዘን በተለያዩ ስሜቶች ውስጥ እንዲከለሉ አድርጓቸዋል፤ በፍርሃታቸውና በሃዘናቸው ቁጥጥር ሥር ሆነዋል። መንፈስ ቅዱስ ሕይወታችንን እንዲሞላ በምንጋብዝበት ጊዜም የሚያደርገው ተመሳሳይ ነገር ነው።

ስለዚህ በመንፈስ ቅዱስ መሞላት ማለት በመንፈስ ቅዱስ ቁጥጥር ሥር መሆን ማለት ነው። የአስተሳሰብ ችሎታና ስሜቶች እንዲሁም ፈቃድና የራስ ኃይል የእግዚአብሔርን ዕቅዶች መፈጸሚያ እንዲሆኑ ለመንፈስ ቅዱስ ተሰጥተዋል ማለት ነው። በተፈጥሮ የሚገኙ የመሪነት ችሎታዎች በመንፈስ ቅዱስ ቁጥጥር ሥር ሲውሉ ይቀደሳሉ፤ ከፍተኛ ኃይልም ያገኛሉ። መንፈስ ቅዱስ በአገልጋዩ ሕይወት ውስጥ አሳዛኝና ተቃዋሚ ነገር ካልገጠመው አገልጋዩን ፍሬያማ ያደርገዋል፤ ለክርስቶስ በሚሰጠው አገልግሎት አሸናፊና ማራኪ ያደርገዋል፤ ስለክርስቶስ ለሚሰጠውም ምስክርነት ኃይል ይሰጠዋል። ፍሬያማ አገልግሎት በመንፈስ ቅዱስ ከተሞሉና በቁጥጥሩ ሥር ከሚኖሩ ሰዎች ሕይወት የሚገኝ ውጤት ነው፤ ዮሐ.7፡37-39።

አንድ ምሁር ስለ መንፈስ ቅዱስ ሙላት ሲያትት እንዲህ ብሏል «ብዙ ሰዎች ከሚወዱት ኃጢአት ለመላቀቅ ሳይፈቅዱ በመንፈስ ቅዱስ ሊሞሉ ይጸልያሉ፤ መልካሙንና ክፉውን መለየት የተለማመደና በክርስትና ሕይወቱ የበሰለ አገልጋይ ደግሞ ይህንን ሁኔታ ተመልክቶ ያዝናል። መንፈስ ቅዱስ በውስጡ እንዲኖርበት የሚፈልግ ሰው በሕይወቱ ተሰውረው ከሚገኙት ኃጢአቶች ሁሉ መላቀቅ አለበት። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንደተገለጸው በልቡ ውስጥ የሚገኘውን ከእግዚአብሔር ባሕርይ ጋር የማይስማማውን ማናቸውንም ነገር ማስወገድ አለበት። በእርሱ ውስጥ ክፉት ዕድሜ ሊኖረው አይገባም፤ እግዚአብሔር የሚጠላቸውን ነገሮች እንደ ቀላል መቁጠር የለበትም።

በመንፈስ ቅዱስ መሞላት ለመንፈሳዊ አገልጋይነት እጅግ አስፈላጊና መጓደል የሌለበትም ነው። እያንዳንዳችንም በመንፈስ ልንሞላ የምንችለው በጥማታችን መጠን ነው።»

# ምዕራፍ 10

## አገልጋይና ጸሎቱ

«ልመናና ጸሎት ምልጃም ሁሉ እንዲደረጉ ከሁሉ በፊት እመክራለሁ፤» 1ጢሞ.2፡1።

መንፈሳዊ አገልጋይ በሌሎች ነገሮች ሳይሆን በጸሎት ረገድ ከሚማራቸው ሰዎች ሁሉ ቀደምት ሆኖ መገኘት አለበት። ቢሆንም የበሰለና ያደገ ክርስቲያን ዘወትር በጸሎቱ የማያቋርጥ ዕድገት ማሳየት እንዳለበት አይዘነጋም፤ በጸሎቴ ከፍተኛውን ደረጃ ደርሼበታለሁ ብሎም አያስብም። አንድ ምሁር ጸሎትን በማስመልከት ሲናገር «አንድን ሰው ማዋረድ ከፈለግሁ ስለ ጸሎቱ እጠይቀዋለሁ፤ እየተጸጸተ ስለ ራሱ እንዲናዘዝ የሚያደርገው ከጸሎት የበለጠ ነገር የለም» ብሏል።

ጸሎት ከሁሉ ይበልጥ ጥንታዊና በአጠቃላይ ከሃይማኖት ጋር የተያያዘ ጉዳይ ነው። ጸሎት የአነጋገር ብስለትን በማይጠይቅ መንገድ በቀላል አገላለፅ በአንድ ጊዜ ሊቀርብ የሚችል ነው፤ ከሁሉ ይልቅ ታላቅ በሆነው በእግዚአብሔር ፊት የሚቀርብ በመሆኑ ጥልቅ የሆኑና የማይደረስባቸውን ነገሮች ይነካል። ጸሎት ለክርስቲያን እጅግ አስፈላጊ እስትንፋሱ ነው።

ነገር ግን በአንጻሩ ብዙዎቻችን ለመጸለይ ጊዜ የለንም ብለን ምክንያት እንፈጥራለን። በተፈጥሯችን ወደ እግዚአብሔር ፊት ለመቅረብ አንናፍቅም። ጸሎት ከፍተኛ ዋጋ አለው፥ ኃይል የተሞላ ነው፥ አስደሳች ነገር ነው ብለን የምንመሰክረው በከንፈራችን ብቻ ነው። ከበሰለ መንፈሳዊ ሕይወት በፍጹም መለየት የሌለበት አስፈላጊ ነገር ነው እያልን በአፋችን እንናገራለን። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተደጋግሞ የተነገረና በርካታ በሆኑ ምሳሌዎችም እውነተኛነቱ የታየ ነው። ቢሆንም አብዛኛውን ጊዜ መጸለይ ሲያቅተን ይታያል።

እስኪ እንደ እኛ ተመሳሳይ ችግር የነበረባቸውን ተፈጥሯዊ ቸልተኝነታቸውን በማሸነፍ ኃይለኛ የጸሎት ሰዎች ሊሆኑ የቻሉትን ሰዎች ምሳሌነት እንመልከት።

የሳሙኤል ቻድዊክ የሕይወት ታሪክ ጸሐፊ ባቀረበው መጽሐፍ ውስጥ፡- «ቻድዊክ ጸሎት የሚወድ ሰው ነበረ። በየጧቱ ወደ አሥራ ሁለት ሰዓት ገደማ ከእንቅልፉ ይነቃል። ለብቻው ወደሚጸልይበት ወደ አንዲት የጸሎት ክፍል በመሄድ እስከ ቁርስ ሰዓት ድረስ ይጸልያል። በግሉ የጥሞና ጊዜ የነበረው ሰው በመሆኑ በጉባዔ የሚያደርጋቸውም ጸሎቶች እጅግ ኃይለኛ ነበሩ። በሚጸልይበት ጊዜ እግዚአብሔር አንድ ነገር ያደርጋል በማለት የማያቋርጥ ተስፋ ነበረው። በሕይወቱ ዘመን መጨረሻ ላይ ለትንሽ ጊዜ እየሠራሁ የበለጠ ብጸልይ ደስ ይለኝ ነበር፤ ከልቤ ጥልቅ ጸሎት ብጸልይ ለእኔ የተሻለ ነበር ብሏል» የሚል ሃሳብ ይገኝበታል።

አንድ ክርስቲያን ሲናገር «ልጸልይ በምነሣበት ጊዜ ልቤ ወደ እግዚአብሔር ለመሄድ የማይታዘዝ ሆኖ አገኘዋለሁ፤ ልቤ ወደ እግዚአብሔር በሚቀርብበት ጊዜ ደግሞ ከእግዚአብሔር ጋር ለመቆየት የማይታዘዝ ይሆናል» ብሏል። ራስን ለሥነ ሥርዓት ማስገዛት

መለማመድ የሚያስፈልገው በዚህ ጊዜ ነው። በዚሁ አጋጣሚ ይህ ሰው በሰጠው ምክር «እንዳትጸልዩ የሚያደርጋችሁ ነገር በሚገጥማችሁ ጊዜ አትማረኩለት፤ ችግሩን ተዋግታችሁ ጸሎት ለመጸለይ ከፍተኛ ጥረት አድርጉ፤ ለመጸለይ አልችልም ብላችሁ በምታስቡበት ጊዜ እንኳን ይህንን አድርጉ።»

እንደሌሎቹ ችሎታዎች ሁሉ ጸሎት የማድረግ ችሎታ ለማግኘት ብዙ ጊዜ ይጠይቃል፤ ይህንን ችሎታ ለማግኘት የምናጠፋው ጊዜ የጸሎትን ጥቅምና አስፈላጊነት የተረዳን የመሆናችን እውነተኛ መለኪያ ነው። ይበልጥ ጠቃሚ ነው ብለን ለምናስበው ነገር ጊዜ ለማግኘት ከፍተኛ ጥረት እናደርጋለን። ለጸሎት የተመደበውን ጊዜ የመቀነሻ ምክንያት የሥራዎች ብዛት ሊሆን ይችላል። ሥራ ይበዛበት የነበረው ማርቲን ሉተር ብዙ እንዲጸልይ የሚያስገድደው ተጨማሪ ሥራ የመሥራቱ አስፈላጊነት ነበረ። አንድ ቀን በማግስቱ ምን ዓይነት ሥራ እንደሚኖረው ለቀረበለት ጥያቄ መልስ ሲሰጥ «ከንጋት እስከ ምሽት ድረስ ሥራ ሞልቷል። ብዙ ሥራዎች መሥራት ስለሚያስፈልገኝ የመጀመሪያዎቹን ሦስት ሰዓቶች መጸለይ አለብኝ» ብሏል። ስለ ጸሎት ጠቃሚነት ያለን አመለካከት ጌታ ኢየሱስ ለጸሎት ከሰጠው ግምት ጋር ቢቀራረብ ብዙ ሰዓቶች ልንጸልይ እንገደድ ነበር።

ጸሎት ከአስተሳሰብ ጋር የተያያዙ ችግሮችን ሊያመጣ የሚችል መሆኑ እውነት ነው። የጸሎትን ጥቅምና ፍሬያማነት የሚጠራጠሩ ሰዎች ግን አብዛኛውን ጊዜ ጠቃሚነቱን ፈትነው የማይረዱና ጸሎት ለማድረግ አስፈላጊ የሆኑትን ነገሮች መፈጸም የማይችሉ ሰዎች ናቸው። ጸሎትን የሚያስተምር ምንም ዓይነት ፍልስፍና የለም። ጸሎት ለማድረግ አስፈላጊ የሆኑትን ነገሮች የሚያሟላ ሰው ግን ጸሎቱ በሚያገኛቸው መልሶችና ከእግዚአብሔር ጋር ባለው ግንኙነት አከራካሪ ባልሆኑ መንገዶች ለችግሮቹ ሁሉ ምላሽ ያገኛል።

የጸሎት አስፈላጊነት የተመሠረተው በኢየሱስ ምሳሌነት ላይ ስለሆነ መንፈሳዊ አገልጋይ ስለ ጸሎት ሕይወት ምሳሌ ማግኘት ሲሻ የጌታ ኢየሱስን ሕይወት መመልከት ያስፈልገዋል። ጸሎት የማያስፈልገው ሰው ቢኖር ኖሮ ኃጢአት ያልነበረበት የሰው ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስ አይጸልይም ነበር፤ ስለ ጸሎትም አያስተምርም ነበር። በኢየሱስ ሕይወት ውስጥ የምንመለከተው ግን ከዚህ የተለየ ነው፤ ጸሎትን እንደ ዋና ነገር በመቁጠር በተደጋጋሚ አስተምሯል። ሥነ ምግባራዊ ተግባሩን በሚመለከት ኢየሱስ የነበረው ራዕይ ብሩህ ሆኖ እስከ መጨረሻ እንዲዘልቅ ያደረገው ጸሎቱ ነበር። ኢየሱስ ፍጹምና ታላቅ መሥዋዕትነት ይጠይቅ የነበረውን የአባቱን ፈቃድ እንዲፈጽም ያስቻለው ጸሎቱ መሆኑን እናያለን። ኢየሱስን በተራራ ላይ የመለወጥ ተአምር ተሳታፊ ያደረገው ጸሎቱ ነበር። ኢየሱስ ጸሎትን የተመለከተው ሊቀር እንደሚችል ተጨማሪ ነገር ሳይሆን እንደ አስደሳችና አስፈላጊ ነገር ነው።

በሉቃስ 5፡16 ውስጥ ኢየሱስ በየዕለቱ ወደ ምድረ በዳ ሄዶ ይጸልይ እንደነበር እንመለከታለን። ወንጌላዊው ይህንን የጻፈው ኢየሱስ አንድ ቀን የፈጸመውን ለመግለጽ ሳይሆን ብዙ ጊዜ በመደጋገም የፈጸመውን ለማመልከት ነው። ጸሎት ለማድረግ ወደ አንድ ቦታ መሄድ የኢየሱስ ልምድ ነበር። ኢየሱስ ጸሎት ለማድረግ ከሰዎች ተለይቶ ማንም ወደማይገኝበት ወደ ምድረ በዳ ይሄድ ነበር። እጅግ ብርቱ መንፈሳዊ ኃይል የተሰጠው ኢየሱስ የጸሎትን አስፈላጊነት ተረድቶ የደከመውን መንፈሱን ለማደስ የብርታት ምንጭ ወደሆነው ወደ ጸሎት መምጣቱ የሚያስደንቅ ነገር ነው። አድናቆታችንን እጅግ ከፍተኛ የሚያደርገው የሕይወት ልውል ዘለዓለማዊ ቃልና የእግዚአብሔር አንድ ልጅ ክርስቶስ በችግር ጊዜ ረዳት የሆነውን ጸጋ ለማግኘት ወደ እግዚአብሔር ዙፋን በልመና መቅረቡ ነው።

ክርስቶስ ሌሊቱን ሙሉ የሚጸልይበት ጊዜ ነበረ፤ ሉቃ.6፡12። ከአባቱ ጋር ያልተቋረጠ ግንኙነት እንዲኖረው ከመንጋቱ በፊት ቀደም ብሎ ይነሣ ነበር፤ ማር.1፡35። በሕይወቱ አንድ ታላቅ ነገር ሳይገጥመው በፊት ልዩ ጸሎት ያደርግ ነበር፤ ለምሳሌ ሉቃ.5፡16፡- «ወደ ምድረ በዳ ፈቀቅ ብሎ ይጸልይ ነበር» የሚለው ሐረግ ልማዱን ያመለክታል። በቃሉም ሆነ በምሳሌነቱ በሚፈጽማቸው ተግባራት በብቸኝነት የመጸለይን አስፈላጊነት ለደቀ መዛሙርቱ አሳይቷቸዋል፤ ማር.6፡46፤ ሉቃ.9፡28። ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን ለመምረጥ የፈጸመው ድርጊት ሰዎችን ለተወሰኑ መንፈሳዊ አገልግሎቶች የመምረጥ ኃላፊነት ለተጣለበት ሰው ብሩህ ምሳሌ ነው።

ጌታ ኢየሱስም ሆነ ለእርሱ ሲል እስረኛ የነበረው አገልጋይ ጳውሎስ እውነተኛ ጸሎት በመዝናናት የሚገኝ ደስታ ብቻ አለመሆኑን በግልጽ አመልክተዋል። እውነተኛ ምልጃ መሥዋዕትነት ነው። ኢየሱስ ይህን ያህል ሳይደክም ብዙ ከባድ ሥራዎችን ሠርቷል። ስላደረጋቸው ጸሎቶች ግን «ከብርቱ ጩኸትና ከእንባ ጋር ጸሎትንና ምልጃን አቀረበ» ተብሎ በዕብ.5፡7 ተነግሮለታል።

የጳውሎስና የኤጳፍራ ትግልና ትንቅንቅ እኛ ከምናደርገው ጋር ቢነጻጸር በእውነት ሳያሳፍረን አይቀርም። ጳውሎስ በቆላስያስ ለነበሩት አማኞች «ኤጳፍራ ሁልጊዜ ስለ እናንተ በጸሎቱ ይጋደላል» ብሎ ጽፎላቸዋል። በተጨማሪም ለእነዚሁ ሰዎች «እንዴት ያለ ትልቅ መጋደል እንዳለኝ ልታውቁ እወዳለሁ» ብሎ ጽፏል። ሕመምና ተጋድሎ የሚሉት ቃላት የወጡት ከአንድ ግሥ ነው። ሥራው ፍጹም እስኪያደክመው ድረስ ተግባሩን የሚፈጽም ሰውን ለማመልከት ቃሉ ይሠራበት ነበር፤ ቆላ.1፡29። ወይም ሽልማት ለማግኘት ሕዝብ በተሰበሰበበት ቦታ የሚወዳደር ሰውን ለማመልከት ይሠራበት ነበር፤ 1ቆሮ.9፡25። ለሕይወቱ የሚዋጋ ወታደርን ያመለክት ነበር፤ 1ጢሞ. 6፡12፤ ወይም የጓደኛውን ሕይወት ከአደጋ ለማዳን የሚታገል ሰውን ያመለክት ነበር፤ ዮሐ.18፡36። ከዚህና ከሌሎቹም መግለጫዎች እንደምንረዳ እውነተኛ ጸሎት ከፍተኛ ጥረት፣ ሥነ ሥርዓትና ትኩረት የሚጠይቅ መሆኑን መመልከት ይቻላል።

ከሰዎች መካከል ስለ ጸሎት በምሳሌነት የሚጠቀሰው ጳውሎስ ስለ ጸሎት ሰፋ ያለ ማብራሪያ ሲሰጥ «እንዴት እንድንጸልይ እንደሚገባን አናውቅም» ብሎ መናዘዙን ማስታወስ የሚያበረታታ ነው። ጳውሎስ በዚሁ ኑዛዜው ላይ ወዲያውኑ «ነገር ግን መንፈስ ራሱ በማይነገር መቃተት ይማልድልናል ልብንም የሚመረምረው የመንፈስ ሃሳብ ምን እንደሆነ ያውቃል፤ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ስለ ቅዱሳን ይማልዳል» የሚለውን መግለጫ ጨምሮበታል፤ ሮሜ 8፡26-28። በምንጸልይበት ጊዜ መንፈስ ከእኛ ጋር ግንኙነት ይመሠርታል፤ የእርሱ ምልጃም በእኛ ልመና ላይ ይጨምራል።

ጸሎት የሚደረግባቸውን መንገዶችና የጸሎትን መሠረታዊ ሃሳቦች መረዳት እንችል ይሆናል፤ ጸሎትን በማስመልከት በተሰጡት ተስፋዎች እውነተኝነት ላይ ከፍተኛ እርግጠኝነት ሊኖረን ይችላል። እየደጋገምን ልንጸልያቸው እንችል ይሆናል። መንፈስ ቅዱስ በጸሎት ውስጥ ያለውን ድርሻ ሥፍራ ካልሰጠነው ግን በዋናው ቁልፍ መጠቀም ተስኖናል ማለት ነው።

ስለ ጸሎት አደራረግ ተከታታይ ትምህርት መስጠት አስፈላጊ ነው። ዋናው አስተማሪም መንፈስ ቅዱስ መሆን አለበት። መንፈስ ቅዱስ ከሚሠራቸው ሌሎቹ ሥራዎች ይልቅ በጸሎት ጊዜ የሚያበረክተው ዕርዳታ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተደጋግሞ ተገልጿል። እውነተኛ ጸሎት

የሚመነጨው መንፈስ ቅዱስ ከነፍስ ጋር በሚያደርገው ግንኙነት ነው። ጳውሎስና ይሁዳ ሁለቱም ፍሬያማ ጸሎት «በመንፈስ መጸለይ» መሆኑን አስተምረዋል። «በመንፈስ መጸለይ» የሚለው መንፈስ ቅዱስ የሚለውን ወይም እርሱ የሚጠራውን ስም በመጥራት መጸለይ ነው ተብሎ ተተርጉሟል። እውነተኛ ጸሎት የሚፈልቀው በክርስቲያን መንፈስ ውስጥ ከሚኖረው ከመንፈስ ቅዱስ ነው።

በመንፈስ መጸለይ ሁለት ዋና ትርጉሞች ሊኖሩት ይችላል። ክርስቲያን ሕይወቱን የሚኖረው በመንፈስ ቅዱስ በመሆኑ በመንፈስ ግዛት ውስጥ ሆኖ መጸለይ ማለት ሊሆን ይችላል። ብዙዎቻችን የምንጸልያቸው ጸሎቶች ግን መንፈሳዊ ሳይሆኑ ሥጋዊ ናቸው። በአዕምሯችን ውስጥ የሚመላለሱና የመንፈስ ቅዱስ ትምህርት ያልሆኑ የራሳችን ሃሳብ ውጤቶች ናቸው። ይህ ጥልቅ ትርጉም ያለው ሃሳብ ነው። በመንፈስ መጸለይ የሰውነትን ብርታትና የአዕምሮን ትብብር ይጠይቃል፤ ይህ እንቅስቃሴ የሚከናወነው በመንፈስ ቅዱስ ግዛት ውስጥ ነው። የእንደዚህ ዓይነቱ ጸሎት ተግባር የሚከናወነው በሰማያዊው መንግሥት ነው።

እንዲሁም በመንፈስ መጸለይ በመንፈስ ቅዱስ ጉልበትና ኃይል መጸለይ የሚል ትርጉም ሊኖረው ይችላል። «በጸሎትና በልመና ሁሉ ዘወትር በመንፈስ ጸልዩ» ኤፌ.6፡18። ጸሎት ከሰው ችሎታ በላይ የሆነ ሥራ በመሆኑ ከሰው ኃይል በላይ የሆነ ኃይል ይጠይቃል፤ ይህም ኃይል የሚገኘው ከመንፈስ ቅዱስ ነው። መንፈስ ቅዱስ የኃይል መንፈስ እንደሆነ ሁሉ የጸሎትም መንፈስ ነው። የሰው ልብና ሃሳብ ያለው ኃይል ሊያስገኝ የሚችለው ውጤት ሰብዓዊ ውጤት ብቻ ነው፤ በመንፈስ ቅዱስ መጸለይ ግን አምላካዊ ኃይል ያስገኛል።

የመንፈሳዊ አገልጋይነት ኃላፊነት ያለበት ሰው ከጸሎት አንፃር ሥጋዊ ድከመት ሲያጋጥመው መንፈስ ቅዱስ ዕርዳታ ሊሰጠው ደስተኛ ነው። በምትጸልይ ነፍስ ፊት ሦስት እንቅፋቶች ተደቅነው ይገኛሉ። መንፈሳዊ አገልጋይ እነዚህን እንቅፋቶች መወጣት የሚያስችል ኃይል ከመንፈስ ቅዱስ ማግኘት ይችላል። አንዳንድ ጊዜ በደለኛነቱን በማወቁ ከጸሎት ይሸሽ ይሆናል። በመንፈስ ቅዱስ ሲታመን ግን እርሱ ከኃጢአት ወደሚያነፃው እጅግ ኃይለኛ ወደሆነው ወደ ክርስቶስ ደም እንዲቀርብ ይረዳዋል። መንፈሳዊ አገልጋይ በአስተሳሰቡ አላዋቂነት ሊደናቀፍ ይችላል። የእግዚአብሔርን ሃሳብ የሚያውቀው መንፈስ ቅዱስ መንፈሳዊው አገልጋይ የጠበቀውን ያህል ከዚህ ዕውቀት ያካፍለዋል። መንፈስ ቅዱስ ይህንን የሚያደርገው አገልጋዩ የሚጸልየው እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ መሆኑን ወይም አለመሆኑን በግልጽ እንዲያውቅ በማድረግ ነው። እንደገና መንፈሳዊ አገልጋይ በሥጋው ድካም ደንዝዞ በምድራዊ ነገሮች የታሠረ ሊሆን ይችላል፤ የስሜት ሕዋሳቱ ምንም ሊሠሩ በማይችሉበት አካባቢ ይህ ሁኔታ ሊያጠቃው ይችላል። በዚህ ሁኔታ ውስጥ የሚገኝ የአገልጋይ እምነት ከመንፈስ ቅዱስ የተነሣ ሟች ሥጋው ሕይወት ሊያገኝ ይችላል፤ በችግሮቹም ላይ ድል ማግኘት ይችላል።

ጸሎተኛ ሰው ከእነዚህ የግል እንቅፋቶች በተጨማሪ በእርሱ ላይ ተጽእኖና ሃዘን እንዲሁም ጥርጣሬና ተስፋ መቁረጥ ሊያመጣበት በሚፈልገው ሰይጣን ላይ ብልሐት በተሞላ ተቃውሞ ድል ማድረግ ይኖርበታል። ጸሎተኛ ሰው ከችሎታው በላይ የሆኑትን ጠላቶቹን ማሸነፍ እንዲችል መንፈስ ቅዱስን አጋዥ እንዲሆን ተሰጥቶታል።

ከዚህ በላይ የተመለከትናቸው ሃሳቦች ላነበቡዋቸው ለብዙ ሰዎች አዲስ አይደሉም። በጸሎት ጊዜ ኃይል የተሞላውን የመንፈስ ቅዱስን ዕርዳታ ማግኘት የሚቻል መሆኑ ግን ለብዙ ሰዎች እንግዳ ነገር ነው። ታዲያ እኛ በጸሎት ጊዜ በመንፈስ ቅዱስ ዕርዳታ እንተማመናለን? በመንፈስ የመጸለይና ለጸሎት ጥያቄዎቻችን መልሶች የማግኘት ልምድ አለን? አብዛኛውን ጊዜ ስለ ጸሎት በአዕምሯችን የምናውቃቸው እውነቶችና በተግባራችን የምንለማመዳቸው ሥራዎች የተነጣጠሉ ሊሆኑ ይችላሉ።

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ጸሎት መንፈሳዊ ውጊያ መሆኑ በተደጋጋሚ ተገልጿል። «መጋደላችን ከደምና ከሥጋ ጋር አይደለምና፤ ከአለቆችና ከሥልጣናት ከዚህም ከጨለማ ዓለም ገዢዎች ጋር በሰማያዊም ሥፍራ ካለ ከክፋት መንፈሳውያን ሠራዊት ጋር ነው እንጂ» ኤፌ.6፡12። የጸሎት ሕይወት በዚህ ረገድ ሁለት ሳይሆኑ ሦስት ተሳታፊዎች ያሉበት መሆኑ ይታያል። በአንድ በኩል እግዚአብሔር በሌላ በኩል ደግሞ ዲያብሎስ ከጸሎተኛው ሰው ጋር ያሉ መሆናቸው ይታያል። ጸሎተኛ ሰው በራሱ ደካማ ቢሆንም እንኳ በአውሬውና በበጉ መሃከል በሚካሄደው የማያቋርጥ ውጊያ ውስጥ ስልት የተሞላው ተሳትፎ አለው። የጸሎት ሰው ያለው ሥልጣንና ኃይል ከራሱ ያገኛቸው ሳይሆኑ በእምነት ከእርሱ ጋር ግንኙነት ካለው ከድል አድራጊው ከክርስቶስ ያገኛቸው ናቸው። ኢየሱስ በቀራንዮ ላይ ያገኘውን ድል በሰይጣን እሥራት ለታሠሩት አብስሮ የሚያስፈታቸው የጸሎተኛ ሰው እምነት ነው።

አስተውሉ አንባቢ ወንጌሎችን ሲመለከት ኢየሱስን ያሳሰበው የነበረው ክፉ ሰዎችና ሁኔታቸው ሳይሆን ከእነርሱ በስተጀርባ ያለው የክፋት ኃይል መሆኑን መረዳት ይችላል። መልካም አሳቢና ሁልጊዜ ተናጋሪ ከነበረው ከጴጥሮስና ከከዳተኛው ከይሁዳ በስተጀርባ የሰይጣን እጅ ያለ መሆኑን ኢየሱስ ተመልክቷል። ጴጥሮስ መልካም ያሰበ አስመስሎ በድፍረት ላቀረበው ተግሣጽ ኢየሱስ የሰጠው መልስ «ወደኋላዬ ሂድ አንተ ሰይጣን» የሚል ነበር። በአካባቢያችን በኃጢአት ታስረው የዲያብሎስ ምርኮኛ የሆኑ ሰዎች እንመለከታለን፤ መጸለይ ያለብን ስለ እነርሱ ብቻ ሳይሆን እነርሱን ምርኮኛ ያደረጋቸውን ሰይጣንን በመቃወም ነው። ሰይጣን በእነዚህ ሰዎች ላይ የጣለውን የእስራት ገመድ መፍታት አለበት፤ ይህ ሊሆን የሚችለው ግን ክርስቶስ በመስቀል ላይ ካስገኘው ድል በሚመነጨው ኃይል ብቻ ነው። ኢየሱስ ሊያስወግድ የሚመኘው ውጤቱን ሳይሆን ምክንያቱን ነው፤ በዚህ ረገድ መንፈሳዊ መሪም ይህንን አርአያ ሊከተል ይገባል። በዚህ ዓይነቱ ውጊያ ውስጥ የእርሱን ተከታዮች መርቶ ወደ ድል ሊያደርስ የሚችልበትን መንገድ ማወቅ አለበት።

ኢየሱስ ሰይጣንን ቤቱንና ያለውን ንብረት ታጥቆ በሚጠብቅ ኃይለኛ ሰው አስመስሎ አቅርቦታል። ያለው ንብረት ከመወሰዱና ምርኮኞቹ ከመለቀቃቸው በፊት ሰይጣን እራሱ መታሰር ወይም ኃይሉን እንዲያጣ መደረግ አለበት። ሌሎችን ማዳን የሚቻለው ከዚያ በኋላ ብቻ ነው፤ ማቴ.12፡28-29። የዲያብሎስን ሥራ ሊያፈርስ በተገለጸው በኢየሱስ ክርስቶስ ድል አድራጊ ኃይል በመጠቀም ሰይጣንን ኃይል ማሰጣት ማለት ካልሆነ ኃይለኛውን ማሰር ማለት እንግዲያ ምን ማለት ነው? ኃይለኛውን ሰው ብርታቱን ማሳጣት የሚቻለው በቀራንዮ ላይ በተገኘው ድልና ጸሎት ካልሆነ በምን ዓይነት መንገድ ነው? የጌታችንን ትዕዛዝ ቅደም ተከተል ባለመጠበቅ ስህተት ላይ መውደቅ የለብንም፤ አስቀድመን ሰይጣንን ኃይሉን ሳናሳጣው ሌሎችን ከእርሱ እስራት ነፃ እናወጣለን ብለን ተስፋ ማድረግ የለብንም። ከአምላክ የተሰጠንን በእጃችን የሚገኘውን ሥልጣን በድፍረት ልንጠቀምበት ያስፈልገናል። ጌታችን «በጠላትም ኃይል ሁሉ ላይ ሥልጣን ሰጥቻችኋለሁ» ብሎ የተናገረው ለደካማ ደቀ መዛሙርቱ ነው።

አገልጋይነት ሰዎች የመማረክና የማንቀሳቀስ ችሎታ በመሆኑ መንፈሳዊ አገልጋይ ይህንን ማከናወን የሚችልበትን ፍሬያማ መንገድ ዘወትር በንቃትና በትጋት መፈለግ አለበት። ከሃድሰን ቴይለር አባባሎች መካከል በጣም የታወቀው፡- «በእግዚአብሔር አማካይነት በጸሎት ብቻ ሰዎችን ማንቀሳቀስ ይቻላል» የሚለው ነው። እርሱም በሕይወቱ ዘመን ይህን እውነት ደግሞ ደጋግሞ አረጋግጦታል። ሆኖም በዓላማ መስማማትና ዓላማን ያለ ማወላወል በተግባር ላይ ማዋል የተለያዩ ነገሮች ናቸው። ሰዎች በአመራር ላይ ችግር የሚፈጥሩና በቀላሉ የማይመሩ ናቸው። ውስብስብነትና ግትርነት ከተሞላው ከሰው ልብ ጋር ግንኙነት ስላላቸው ነገሮች ከመጸለይ ይልቅ ለአንድ ጊዜያዊ ችግር መጸለይ ይቀላል። መንፈሳዊ አገልጋይ የእግዚአብሔር ፈቃድ ነው ብሎ በሚያምንበት ጎዳና የመምራት ችሎታ ያለው መሆኑን የሚያረጋግጠው በእነዚህ ዓይነት ሁኔታዎች ውስጥ ሲገኝ ነው። መንፈሳዊ አገልጋይ እነዚህን ውስብስብ ችግሮች የሚፈታበትን ቁልፍ እግዚአብሔር በእጁ ሰጥቶታል።

ሰው በእግዚአብሔር ምሳሌ የተፈጠረና ነፃ ምርጫ ያለው በመሆኑ በሁሉ ላይ የበላይነት ሥልጣን ላለው አምላክ ለእግዚአብሔር እሺ ብሎ መታዘዝ እንደመቻሉ ሁሉ እምቢተኛም መሆን መቻሉ ከፍተኛ ክብሩና ግርማው ነው። ይህ ሐቅ ጸሎትን በመማር ላይ ላለ ሰው ትልቅ ችግር ይፈጥርበታል። በጸሎታችን የሰውን ባሕርይ ማስለወጥ ብንችል ለሰውየው የተሰጠውን ነፃ ምርጫ መጣሳችን ነው? እግዚአብሔር የአንድ ሰው ጸሎት ለመስማትና ለመመለስ ሲል የሌላውን ሰው ነፃ ምርጫ ይጥሳል? ጸሎታችን የእግዚአብሔርን ሃሳብ ማስለወጥ ካልቻለ መጸለያችን ለምን አስፈለገ?

ይህንን ችግር ስንመለከት ልናስታውሰው የሚገባን የመጀመሪያው ነገር እግዚአብሔር በሚሠራቸው ሥራዎቹ ዘወትር ከራሱ ጋር ስምምነት ያለው መሆኑን ነው። እግዚአብሔር ባወጣው መርሐግብር ውስጥ ምንም ዓይነት ተጽእኖ ሊኖር አይችልም። የእምነትን ጸሎት ሊመልስ ቃል ከገባ በቃል ኪዳኑ መሠረት ይፈጽመዋል! ይህንን የሚያደርገው ግን የራሱን ባሕርይ በሚያፋርስ መንገድ አይደለም። የገባቸውን ግዴታዎች በሙሉ ይፈጽማል! ራሱን ሊክድ ስለማይችል ሁሉን የሚፈጽመው ከራሱ ጋር በማይቃረን ሁኔታ ነው። ከአንድ የእግዚአብሔር ቃል ወይም ሥራ ጋር የሚጋጭ ሌላ የእግዚአብሔር ቃል የለም።

ምልጃ እግዚአብሔር ካዘዛቸው የጸሎት ክፍሎች አንዱ እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱስ ያስረዳናል። የምልጃ ጸሎት በእግዚአብሔር የታዘዘ በመሆኑ የእግዚአብሔርን ፈቃድ የምንፈጽም ለመሆናችን እርግጠኞች በመሆን ልንጸልይ እንችላለን! የቱንም ያህል ችግሮች ቢኖሩበትም ለዚህ ዓይነት ጸሎት መልስ ማግኘታችን የተረጋገጠ ነው። ነፃ በሆነው የሰው ምርጫና እግዚአብሔር ለሰው በሚሰጠው የጸሎት መልስ መሃከል ምንም ዓይነት ሊፈታ የማይችል ችግር ወይም ቅራኔ አለመኖሩ ለእግዚአብሔር ግልጽ ነው። በሥልጣን ላይ ላሉ ሰዎች እንድንጸልይ የሰጠው ትዕዛዝ ጸሎታችን የአንዳንድ ድርጊቶችን አቅጣጫ ማስለወጥ የሚችል መሆኑን በግልጽ ያመለክታል። አለዚያ ጸሎት ለምን ያስፈልጋል? ስለ ጸሎት ለምናቀርባቸው ጥያቄዎች አርኪ መልስ ብናገኝም ባናገኝም ያለማቋረጥ የመጸለይ ግዴታ አለብን።

ከዚህ በተጨማሪም ስለምንጸልየው ጸሎት እግዚአብሔር ያለውን ፈቃድ ማወቅ እንችላለን። ይህም ሐቅ የእምነት ጸሎት ለመጸለይ የመቻላችን መሠረት ነው። እግዚአብሔር በሚያሳምን መንገድ መረዳት በምንችልበት ሁኔታ ሊናገረን ይችላል። መመሪያ ማግኘት በሚያስፈልጉን ነገሮች ሁሉ ላይ የሚረዳንና የእግዚአብሔርን ፈቃድ የሚያሳየን ቃሉ ነው።

በልባችን ውስጥም እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ የሚማልድልን የመንፈስ ቅዱስ አገልግሎት አለ፤ ሮሜ 8፡26-27። እግዚአብሔር ስለልመናችን ያለውን ፈቃድ በትዕግሥት ስንፈልግ ልመናችን የእግዚአብሔር ፈቃድ መሆኑን ወይም አለመሆኑን መንፈስ ቅዱስ ይነግረናል። ይህ እገዛ ከተስፋ ጸሎት ወደ እምነት ጸሎት እንድንሸጋገር ያስችለናል።

እግዚአብሔር እንድንጸልይ ማንቀሳቀሱና ጸሎታችንን እንድንቀጥል ማበረታታቱ ምላሽ መስጠት የፈለገ መሆኑን ያስገነዝበናል። ሁለት ሰዎች ክርስቲያን እንዲሆኑ ለሐምሳ ዓመታት የጸለየ አንድ ክርስቲያን «እነዚህ ሰዎች ወደ ክርስትና እምነት ይመጣሉ ብለህ ታስባለህ?» ተብሎ የቀረበለትን ጥያቄ ሲመልስ «እነዚህ ሰዎች እንዲያምኑ እግዚአብሔር ባያቅደው ኖሮ ይህንን ያህል ዓመታት እንድጸልይ ያደርግ ነበር?» በማለት እምነቱን ገልጿል። ከእነዚህ ሁለት ሰዎች አንዱ ጸሎተኛው ከመሞቱ ጥቂት ጊዜያት ቀደም ብሎ ሌላው ደግሞ ከሞተ ከጥቂት ጊዜያት በኋላ ክርስቶስን በማመን ሕይወታቸው ተለውጧል።

በምንጸልይበት ጊዜ በመጀመሪያ ደረጃ ግንኙነታችን ከእግዚአብሔር ጋር ሲሆን በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ ከሰዎች ጋር ነው። የጸሎት ዒላማ የእግዚአብሔር ጆሮ ነው። ጸሎት እግዚአብሔር በሰዎች ልብ ውስጥ እንዲሠራ የሚማልድ ሰዎችን የመማረክ ዘዴ ነው። ሰዎችን የሚለውጣቸው ጸሎት ሳይሆን ጸሎታችንን የሚቀበለው እግዚአብሔር ነው። ጸሎት ዓለምን የሚያንቀሳቅሰውን የእግዚአብሔርን ክንድ በማንቀሳቀስ ደኅንነትን ያመጣል።

አንድ አገልጋይ ሰዎችን ለመማረክ ከፈለገ የእግዚአብሔርን እጆች ማንቀሳቀስ መቻል አለበት። እግዚአብሔር እራሱ በሚማልዱ ሰዎች ጸሎት ሰዎችን ሊለውጥ የሚችል መሆኑን በግልጽ ተናግሯል። ብልጥ የነበረው ያዕቆብ ከእግዚአብሔርና ከሰዎች ኃይል ማግኘት ከቻለ ፈቃደኛ የሆነ አገልጋይ ተመሳሳይ ኃይል ማግኘት የማይችልበት ምን ምክንያት አለ? ዘፍጥ.32፡8።

ፍሬያማ ጸሎት መጸለይ የሚቻለው ከእግዚአብሔር ጋር ትክክለኛ ግንኙነት ሲኖር ነው። ጸሎቶች መልስ ሊያገኙ የማይችሉባቸው ምክንያቶች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ተጠቁመዋል፤ እነዚህ ምክንያቶች አማኞች ከእግዚአብሔር ጋር ባላቸው ግንኙነት ላይ ያተኩራሉ። የአማኝ ጸሎት በራስ ጥቅም ላይ ያተኮረ ልመና መሆን የለበትም። አማኝ ቅድስና በጎደለው ፍላጎት ተነሣሥቶ መጸለይ የለበትም። ያልተወገዱ ኃጢአቶች በአማኝ ሕይወት ውስጥ ከተገኙ እግዚአብሔር ጸሎትን እንዳይሰማ ያደርጋል። ወደ እግዚአብሔር የሚመጣ ሁሉ በቃሉ መሠረት መቅረብ አለበት። ጸሎት ሲደረግ ምንጊዜም ዋና ዓላማው ለእግዚአብሔር ክብር መሆን አለበት።

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ታሪካቸው የተገለጸው ታላላቅ አገልጋዮች ታላቅ ሊሆኑ የቻሉት በጸሎት ነው። ታዋቂነት ያተረፉት በአስተሳሰባቸው ብሩህነትና በሀብታቸው ብዛት ሳይሆን የእግዚአብሔርን ኃይል በጸሎት ብርታት ማዘዝ ስለቻሉ ነበር።